# የግብረገብ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 5ኛ ክፍል

### አዘጋጆች

ፍራንኦል ዋቅጅራ

ታምራት ለገሠ

ተስፋዬ አመኑ

### አርታኢዎች

ግሩም ጥበቡ

ታምሩ ገለታ

### ገምጋሚ

ደረጄ መኮንን

### ግራፊክስ

ታደሰ ድንቁ

### ገላጭ ስዕል

ብዙአየሁ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2015/2023

ይህ መጽሐፍ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ2015/2023 ተስማምቶ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው። የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ በየትኛውም መልኩ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህ መጽሀፍ በትምህርት ሚኒስቴር አመራርና መነሻነት በሀዋሳ ፣ጅማ፣ አዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡ በመቀጠል በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ቅንጅት ተተርጉሞና ተስማምቶ ተዘጋጀ፡፡

ስለዚህ በዚህ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የዩኒቨርስቲ አዘጋጆችና በክልላችን ላሉ የትምህርት ባለሙያ ተርጓሚዎችና አስማሚዎች በሙሉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋና አለው፡፡

# ማውጫ

ይዘቶች ገጽ

ምዕራፍ 1:የኃላፊነትን መወጣት....1

1.1 የኃላፊነት ምንነት....2

1.2. ኃላፊነትን የመወጣት ምንነት....5

1.3. ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነት....7

1.4. የኃላፊነት ደረጃዎች....10

1.5. ግብረገባዊ የኃላፊነት አይነቶች....13

ምዕራፍ 2: ጠንክሮ የመስራት ባህል....24

2.1. ጠንክሮ የመስራት ባህል ምንነት....25

2.2. የጠንክሮ መስራት ባህል አስፈላጊነት....27

2.3. የጠንካራ ተማሪ የስራ ባህል መገላጫዎች....29

2.4. የማንበብ ባህል....31

2.5. የንባብ ባህልን የሚያዳብሩ ብልሃቶች....34

ምዕራፍ 3: ክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ችሎታ....39

3.1. የትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ጽንሰ ሃሳብ....40

3.2. ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ችሎታ ባህሪያት....42

3.3. ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ልንከተላቸው የሚገቡ ደረጃዎች....45

3.4. የትክክለኛ ወሳኔ አስፈላጊነት....51

3.5. ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት እንቅፋቶች....53

ምዕራፍ 4: የአካባቢ እንክብካቤ....57

4.1 የአካባቢን ምንነት መረዳት....57

4.2. የአካባቢ ጥበቃ ምንነት....58

4.3. የአካባቢ ጥበቃ አስፈላጊነት...59
4.4. አካባቢን የመንከባከብ መንገዶች...61
4.5. አካባቢን ባለመንከባከብ የሚከሰት ጉዳት...63
ምዕራፍ 5: የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር ...68
5.1. የማህበራዊ ሚዲያ ምንነት...69
5.2 የማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነት...70
5.3. የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር...71
5.4. የማህበራዊ ሚዲያ አላግባብ የመጠቀም ጉዳቶች...74
ምዕራፍ 6: የባህል ትስስር...78
6.1. የባህል ግንኙነቶች ምንነት...78
6.2. የባህል ትስስር አስፈላጊነት...81
6.3. ባህል እና ሉላዊነት...83
6.4. የባህል ትስስር መገለጫዎች...86

# ምዕራፍ 1

# የኃላፊነትን መወጣት

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የተጠያቂነት ጉዳዮችን የሚያወሱ አራት ንኡሳን ትምህርቶችን አካቷል። እነሱም፡- የኃላፊነት ምንነት፣ የኃላፊነት አስፈላጊነት፣ የኃላፊነት ዓይነቶች እና ሥነምግባርን መተግበር ናቸው። በእነዚህ ንኡሳን ትምህርቶች እንደ አስፈላጊነቱ የሚጠበቅብህን/ሽን እንድታደርግ/ጊ፣ ምርጥ ልምዶችን እንድታከናውን/ኚ፣ ለድርጊቶችህ/ሽ ኃላፊነት እንድትወስድ/ጂ የሚያግዝ ትምህርት ትማራለህ/ሪያለሽ። በዚህ መሰረት ትምህርቶቹ ለበጎ ስራ ምስጋና እና ሽልማት እንዳለ ሁሉ ለመጥፎ ስራም ትችት እንደማይቀር ያስገነዝብሃል/ሻል።

### ጽንሰሀሳቦችና ቁልፍ ቃላት፡

ኃላፊነት፣ ተጠያቂነት፣ ቁርጠኝነት፣ ሰዎችን መርዳት፣ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም፣ ግብር መክፈል፣ የትራፊክ ህጎችን ማክበር

## በምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነትን መገንዘብ፤
- የኃላፊነት ደረጃዎችን መለየት፤
- የህብረተሰቡን ስነምግባር እና ስነምግባርን የመተግበር እሴቶችን ማድነቅ፤ ማክበር፤
- ከአንድ ሰው የሚጠበቅ የሞራል ኃላፊነትን መዘርዘር።

# 1.1 የኃላፊነት ምንነት

## ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ኃላፊነት ምን እንደሆነ ታብራራለህ/ ሪያለሽ፤
- በቤተሰብህ/ሽ ውስጥ ያለህን/ሽን ኃላፊነት ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄ

- እስኪ በቤተሰብህ/ሽ ውስጥ ያለህን/ሽን ኃላፊነት ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ አብራራ/ሪ።

ኃላፊነት እራስን መቻል፣ ጥሩ ምርጫዎችን ማድረግ እና ለሚወስዷቸው እርምጃዎች ኃላፊነት መውሰድ ናቸው።. ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች የሌሎችን ደህንነት ከፍ አድርገው ይመለከታሉ፤ ዓለምን የተሻለ የመኖሪያ ቦታ ለማድረግ የሰው ልጆች የሚጫወቷቸውን ሚናዎች ይገነዘባሉ።

### የጉዳይ ጥናት፡ የአባትና ልጅ ቃለ ምልልስ

ልጅ: "አባዬ፣ ሂጀ ጫላ ጋር እጫወታለሁ."

አባት፡ "የትምህርት ቤት የደንብ ልብስህን አጥበሀል/ሻል?"

ልጅ፡ "አይ፤ ስመለስ አጥባለሁ"

አባት፡ "በዳሳ፣ የትምህርት ቤት የደንብም ልብስህን ማጠብ የአንተ ኃላፊነት ነው። አስቀድመህ የቤት ውስጥ ኃላፊነትህን መወጣት ይገባሃል። የደንብ ልብሶችህን ካጠብክ በኋላ ወደ ጫላ መሄድ ትችላለህ።"

## ተግባር 1

ከላይ በቀረበው ውይይት ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. በዳሳ በቤተሰቡ ውስጥ ሃላፊነቶች አሉት?
2. የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች በቤተሰባቸው ውስጥ ምን አይነት ሃላፊነቶች ሊኖራቸው ይገባል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያለሽ?



ምስል 1.1 ማንኛውንም ስራ በኃላፊነት መስራት

ኃላፊነት ሁሉም ተማሪዎች የድርሻቸውን እንዲወጡ በትኩረት ሊያጤኑት የሚገባ ጉዳይ ነው። በምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጪ ስኬታማ ለመሆን የሚከተሉት ሃላፊነቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

- ራስን መቻል፤
- በራስ መተማመን፤
- ቃልን መጠበቅ፤
- ሚና መወጣት፤
- ለተፈጸመ ነገር ኃላፊነት መውሰድ፤

- ስህተቶችን ለመቀበል እና ለማረም ዝግጁ መሆን፤
- በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ እና በሀገር ደረጃ ኃላፊነትን መወጣት።

ተማሪዎች ሃላፊነታቸውን የሚወጡባቸው አንዳንድ መንገዶች፤

- ለጓደኞች ማሰብ፤
- ለቤተሰብ ማሰብ፤
- ለጎረቤቶች ማሰብ፤
- ማህበረሰብን ለመርዳት በጎ ፈቃደኝነት መያዝ፤
- ስህተትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ።



ምስል 1.2 በበጎ ፈቃደኝነት ሥራ ላይ በንቃት መሳተፍ

## ተግባር 2

1. ከላይ በተዘረዘሩት የኃላፊነት ተግባራት ውስጥ ተሳትፈህ/ሽ ታውቃለህ/ ቂያለሽ? ከተዘረዘሩት ሌላ ምን አደርገህ/ሽ ታውቃለህ/ቂያለሽ?
2. እንደ ተማሪ መደረግ የማይገባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
3. በአካባቢህ/ሽ ልትሳተፍ/ፊ የምትችልባቸው/ ይባቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶችን ዘርዝር/ሪ።

## 1.2. ኃላፊነትን የመወጣት ምንነት

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ተጠያቂነትን መወጣት ምን ማለት እንደሆነ ትገነዘባለህ/ ቢያለሽ፤
- ሃላፊነታችሁን ለመወጣት ልትወስድ/ጂ የሚጠበቅብህ/ሽ ተግባራቶችን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- ለድርጊትህ/ሽ ኃላፊነት ትወስዳለህ/ ጂያለሽ።

ኃላፊነትን መወጣት ማለት ከአንድ ሰው የሚጠበቅ ስራን በአግባቡ መከወን ማለት ነው። ይህም አንተ/ቺ በምታከናውናቸው/ ኺያቸው ስራዎች ይገለጻል፤

ለምሳሌ፡-

- ቤተሰቦችህ/ሽ እጅህን/ሽን እንድትታጠብ/ቢ ይጠብቃሉ። ስለዚህ ሁልጊዜ ከምግብ በፊት እና በኋላ እጅህን/ሽን መታጠብ ኃላፊነትህ/ሽ ነው።
- መምህሮችህ/ሽ የቤት ስራህን/ሽን እንድትሰራ/ሪ ይጠብቃሉ። ስለዚህ የቤት ስራህን/ሽን በአግባቡ ሰርተህ/ሽ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት የአንተ/ቺ ኃላፊነት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ከናንተ የሚጠበቁ ሌሎች ሃላፊነቶችን እንድትወጡ ይጠብቃሉ። ለምሳሌ፡- ቤተሰብህ/ሽ በመንገድ ላይ እንድትጫወት/ቺ አይፈልጉም። ስለዚህ፣ በአደገኛ ቦታዎች ላይ መጫወት የለብህም/ሽም። ይህ ደግሞ የአንተ/ቺ ኃላፊነት ነው።



ሀ) ተማሪዎች ጠንክሮ የመማር ኃላፊነት አለባቸው



ለ) ተማሪዎች ከትራፊክ አደጋ እራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው

ምስል 1.3. ተማሪዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት አለባቸው

## ተግባር 3

ከባልደረባህ/ሽ ጋር በመሆን አንተ/ቺ እንድትሰራ/ሪ የሚጠበቅብህን/ሽን ተግባራት ዘርዝር/ሪ፤ ተግባራቱ እንዴት እንደሚሰሩም አብራራ/ሪ።

እንዲሰሩ የሚጠበቅብህ/ሽ ተግባራት ዝርዝር፡

1.______________________________

2.______________________________

3.______________________________

ስራዎቹ እንዴት እንደሚሰሩ ማብራሪያ፡

1.______________________________

2.______________________________

3.______________________________

# 1.3. ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነት

## ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ኃላፊነት የመወጣትን አስፈላጊነት ታብራራለህ/ሪያለሽ፤
- ለምን ኃላፊነት መወጣት እንደሚያስፈልግ ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- ለፈጸምካቸው/ሻቸው ድርጊቶች ኃላፊነትን ትወሰወዳለህ/ጃለሽ።

ኃላፊነትን ከሚጠይቁ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

☞ **በድርጊት አፈፃፀም ጊዜ ኃላፊነትን መወጣት**


ኃላፊነትን መወጣት ድርጊቱንና የድርጊቱን ውጤቶች የሚያስተሳስር ነው። ኃላፊነት መወጣትን የመገንዘብ አስፈላጊነትን የምንረዳበት አንዱ መንገድ ሃላፊነታችንን ሳንወጣ ስንቀር የሚያስከትልብንን መዘዝ ማወቅ ነው። ኃላፊነትን መወጣት ከሁሉም ሰው ይጠበቃል። ሌሎች ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ከፈለግን እኛም ሃላፊነታችንን መወጣት አለብን። ልንወጣቸው ከሚገቡ አንዳንድ ሃላፊነቶች መካከል የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡-

### ሀ. የሌሎችን መብት የማክበር ኃላፊነት።

ተማሪዎች በሚጫወቱበት ጊዜ ስለ ጓደኞቻቸው መብቶች መጠንቀቅ አለባቸው። ሰዎች መብታችንን ሲጥሱ እንደሚሰማን ሁሉ እኛም የሌሎችንም መብት ስንጥስ እንደሚሰማቸው ማወቅ አለብን።

### ለ. ለአካላችን እና ለልብሳችን ንጽህና ያለን ኃላፊነት

ሰውነታችንን እና ልብሳችንን በንጽህና መያዝ አለብን።



ምስል 1.4. ተማሪዎች ንጽህናቸውን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው

## ሐ. የምንገለገልባቸውን መሳሪያዎች የመንከባከብ ኃላፊነት

➢ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚገለገሉባቸውን መሳሪያዎች ባይንከባከቡ ምን ይከሰታል? ለቤት ቁሳቁሶች ጥንቃቄ ባናደርግስ?

በትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ውጪ ለምንገለገልባቸው መሳሪያዎች አስፈላጊ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። ይህ ደግሞ ከእኛ የሚጠበቅ ኃላፊነት እንደሆነ መገንዘብ አለብን።

### ☞ ስሜታችንን መቆጣጠር

ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት አዎንታዊ ወይም ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ያደርጋል፡ ነገር ግን ሃላፊነታችንን በአግባቡ ካልተወጣን አሉታዊ ወይም መጥፎ ስሜት እንዲሰማን ያደርጋል። አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛ ድርጊት መፈጸም ወይም ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት አስቸጋሪ የሚሆንበት ወይም ሊሳካልን የሚችልበት ጊዜ ይኖራል፤ የዚህም ውጤት አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሊሆን ይችላል። ሃላፊነታችንን በተሳካ ሁኔታ ከተወጣን ጥሩ ውጤት እናገኛለን ወይም ስሜታችን የተረጋጋ ይሆናል። ሌሎች አካላትም እንዲሁ በስራችን ሊረኩ ይችላሉ። ነገርግን፣ ሃላፊነታችንን በአግባቡ ካልተወጣን ስሜታችን ሊጎዳ

ወይም ሊረበሽ ይችላል፣ እንዲሁም ሌሎች አካላት በድርጊታችን ሊበሳጩ ይችላሉ።

## የጉዳይ ጥናት፡ የእግር ኳስ ጨዋታ ገጠመኝ

ለቴራ ከጓደኛው ፋይሳ ጋር ኳስ ይጫወት ነበር። ለቴራ እራሱን በመንደሩ ውስጥ ምርጥ ተጫዋች ነኝ ብሎ ያስባል። በዚህ የተነሳ ኳሱን አጠንክሮ ሲመታ ኳሱ ከአጥሩ በላይ ሄዶ የጎረቤታቸውን ቤት መስኮት መስታወት ሰበረ። ለቴራ እና ፈይሳ በጣም ደነገጡ። ፈይሳ እንሸሻለን ብሎ ሮጠ። ለቴራ ግን መሮጥ አልፈለገም። ወደ ቤቱ ባለቤት አቶ ገመዳ ሄዶ፣ “አቶ ገመዳ፣ በጣም አዝናለሁ፣ ትኩረት ሳልሰጥ መጫወቴ የእኔ ጥፋት ነው። አባቴ የተሰበረውን ሊተካ ይችላል።” ሲል ይቅርታ ጠየቀ።

### ተግባር 4

ከላይ ባለው የጉዳይ ጥናት ላይ ተመስርታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩ።

1. ፈይሳ ለምን ሮጠ? ምን ማድረግ ነበረበት?
2. ለቴራ ምን አደረገ?
3. ለቴራን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

# 1.4. የኃላፊነት ደረጃዎች

## ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የኃላፊነት ደረጃዎችን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፣
- በኃላፊነት ደረጃዎች መካከል ያለውን ልዩነት ትለያለህ/ሽ።

የሰው ልጅ እውቀት እና ጥበብ ያለው ፍጡር ነው። እኛ 'ከፍጡራን ሁሉ የበላይ ነን' ካልን እውቀታችንን እና አቅማችንን በአግባቡ መጠቀም አለብን። ለድርጊታችንም ተጠያቂ መሆን ይኖርብናል ወይም ድርጊቶቻችንን በኃላፊነት መፈጸም ይገባናል። ከነዚህም ሃላፊነቶች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

### ሀ. ግለሰባዊ ሃላፊነቶች

ግለሰባዊ ሃላፊነቶች ከግለሰብ ባህሪያትና እና ልማዶች ጋር የተያያዙ ናቸው። ከነዚህ መካከልም ጥቂቶቹ፤

- በአክብሮት መናገር፤
- የሌሎችን ስሜት ማክበር፤
- የትምህርት ቤቶችን የጊዜ ሰሌዳዎች፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን መከተል፤
- መምህራን የሚሰጡንን ስራዎችን በወቅቱ ማጠናቀቅ፤
- ምግብን አለማባከን፤
- እውነትን መናገር፤
- አለመዋሸት፤
- የግል ንፅህናን እና ጤናን መጠበቅ፤
- ለጓደኛ ታማኝ መሆን፤
- አለመስገብገብና ያለንን ለሌሎች ማጋራት፤
- ጎጂ የሆኑ ቁሶችን አለመጠቀም፤

- በእድሜ ከገፉ ሰዎች፣ ከቤተሰብ እና ከመምህራን ምክር መቀበል፤
- የራስ ቤትን እና የትምህርት ቤትን ንፅህና መጠበቅ።

## ለ. በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ደረጃ የምንወጣቸው ሃላፊነቶች

ቀጣይነት ያለው ህይወት ለመኖር ሁሉም ሰው በቤተሰቡ እና በማህበረሰቡ ውስጥ የራሱን ኃላፊነት መውሰድ አለበት። በቤተሰብ ውስጥ የተለያየ የዕድሜ ደረጃ ያላቸው የቤተሰብ አባላት አሉ። እነዚህ የቤተሰብ አባላት ከቤተሰብ እና ከማህበረሰቡ ጋር ተስማምተው ለመኖር ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት አለባቸው። የበለጸጉና ደስተኛ ቤተሰቦችን እንዲሁም ማህበረሰቦችን ለማፍራት ስራቸውን በሚገባ መስራት አለባቸው። ስለዚህ ሁሉም የቤተሰብ አባላት እና ማህበረሰቦች የማህበረሰቡን ስነ ምግባር እና ወጎች ማክበር አለባቸው። እነዚህ የማህበረሰብ እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፡-


- በማንኛውም ሥራ ቤተሰብን መርዳት፤
- መከባበር፤
- ለአረጋውያን እና ለታመሙ ሰዎች እንክብካቤ ማድረግ፤
- ልጆችን መጠበቅ፤ መልካም ስነ ምግባርን ማስተማር፣ በትክክለኛው መንገድ መምራት
- የግል፣ የቤተሰብ እና የማህበረሰብን ስራ ማክበር፤



ምስል 1.5 ተማሪዎች በአቅማቸው ወላጆቻቸውን በስራ የማገዝ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ሐ. በሀገር ደረጃ የምንወጣቸው ሃላፊነቶች

እንደአንድ ዜጋ እና እንደሀገር አባል ለሀገራችን ቅድሚያ በመስጠት ሀገራችን የምትፈልገውን ሀላፊነት መወጣት አለብን። ይህም ሀገራችን እንድታድግ እና የተሻልን ዜጋ እንድንሆን ያደርገናል። እነዚህ ሃላፊነቶች ከዚህ በታች ባለው ሥዕል ውስጥ ተመላክተዋል።




ምስል 1.6 የዜግነት መገለጫዎች

## ተግባር 5

1. ሦስቱ የኃላፊነት ደረጃዎች እነማን ናቸው?
2. የግለሰብ ደረጃ ሃላፊነቶችን ዘርዝር/ሪ።

# 1.5. ግብረገባዊ የኃላፊነት አይነቶች

## ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኃላ፡-

- ግብረገባዊ ኃላፊነት ምን እንደሆነ ታብራራለህ/ ሪያለሽ፤
- ስልጣኔ በምን እንደሚገለጽ ትዘረዝራለህ/ ሪያለሽ፤
- በህብረተሰብ ውስጥ ያለህን/ሽን ግብረገባዊ እሴቶች ትለያለህ/ሽ።

የሰው ልጅ ማህበራዊ ነው። በማህበራዊ ህይወት ውስጥ መከባበር አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ በኦሮሞ ማህበረሰብ መዋቅር ውስጥ የሀገር ሽማግሌዎች፣ እናቶች እና አባቶች፣ አያቶች፣ የገዳ አባቶች እና ሃዳ ሲቄዎች የተከበሩ ናቸው። ሀሳባቸው፣ ደረጃቸውና በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና ይከበራል። ይህ አክብሮት ለእነሱ ያለንን አክብሮት ያሳያል። ኦሮሞው እነዚህን የተከበሩ ማህበረሰባዊ መዋቅሮች ዋዩ ይላቸዋል። ዋዩ መሆናቸውን ለመግለጽ እናት እና አባት የተከበሩ ናቸው፣ ሽማግሌዎች የተከበሩ ናቸው፣ የገዳ አባቶች የተከበሩ ናቸው፣ የሲንቄ እናቶች የተከበሩ ናቸው። ስለዚህም በመከባበር ወይም በዋዩ ሥርአት ኦሮሞ ጥሩ ቤተሰብ፣ ማህበራዊ እና የህዝብ ግንኙነት እንዲኖረው አስችሎታል። ስለዚህ፣ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ሰዎች እርስ በእርሳቸው የሚኖራቸው ግንኙነት የአንድን ሰው ኃላፊነት መወጣት እና አለመሟላት ላይ ተንጸባርቋል። ለምሳሌ በህብረተሰብ ውስጥ ያለንን ሀላፊነት መወጣት የምንችልባቸው አንዳንድ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው።

- ቃል ኪዳንን መጠበቅ፤
- ሌሎችን መርዳት፤
- የጋራ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም፤
- በህብረተሰቡ ውስጥ በንቃት መሳተፍ፤
- በወቅቱ ግብርን መክፈል፤

- የትራፊክ ህጎችን ማክበር፤
- ዋዩማ እና ወዘተ።

## ሀ. ቃልኪዳንን መጠበቅ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ቃል ኪዳን ማለት ምን ማለት ነው?

ቃልክዳን ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የተስማሙበት ነው። ቃልን መጠበቅ ስምምነትን መፈጸም ነው። የተስፋ ቃልን የማክበር ኃላፊነት ለመለማመድ አምስት መንገዶች አሉ። ናቸው:

- ቃሌን መጠበቅ አለብኝ፤
- ሰበብ አያቀርብም፤
- ስራዬን በደንብ እሰራለሁ፤
- የተሳሳትኩትን አስተካክላለሁ፤
- ሥራዬን አውቃለሁ፤ እሰራዋለሁ።

ለምሳሌ  ከኦሮሞ ልጃገረዶች ወዳጅነት አኳያ እነዚህን የተስፋ ቃሎች የማክበር መንገዶችን ተመልከት።

አዶዬ፤ የኦሮሞ ልጃገረዶች እርስ በርስ ያላቸውን እውነተኛ ፍቅር እና አክብሮት ለማሳየት የሚመሰርቱት ጓደኝነት ነው። በእድሜም ሆነ በትውልድ ቅርበት ያላቸው የኦሮሞ ልጃገረዶች ተስማምተው እርስ በርስ በመዋደድና በመቆም ጓደኛ ይሆናሉ። ጓደኝነታቸውን ላለማፍረስም ይስማላሉ። ቃል ኪዳናቸውም የራሱ ሕግ አለው። በመጀመሪያ ሁለቱ ሰዎች ተጨባበጡ እና እርስ በርሳቸው ተማማላሉ።

ሀ፡ አዶዬ አዶዬ

ለ፡ አዬ ዬ!

ሀ፡ ስምሽን እንደገና ባነሳ ሞት ስሜን ያንሳ።

ለ፡ እኔም እንደዛው

ብለው በቃል ኪዳን ተስማምተው አደዬ ይባላሉ እንጂ በስም አይጠራሩም። በዚህ መሠረት ጓደኝነታቸው የበለጠ እየጠነከረ ይሄዳል።

## ለ. ሌሎችን መርዳት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ከቤተሰብዎ ውጭ ያሉ ሰዎች ረድተዎት ያውቃሉ?

ሌሎችን መርዳት በጣም አዎንታዊ ተግባር ነው። ለተረዱት ብቻ ሳይሆን ለሚረዱትም ደስታን ይሰጣል። እርስ በርስ መረዳዳት ጥሩ ግንኙነት እና ደስተኛ እና አንድነት ያለው ማህበረሰብ ይፈጥራል። ሰዎች በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በጊዜ፣ በሃሳብ እና በጉልበት እርስ በርስ መረዳዳት ይችላሉ። ሌሎችን መርዳት፤

- ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የህይወት ትርጉምም ነው፤
- ምቹ የመኖሪያ አካባቢን ይፈጥራል፤
- ለሌሎች ደግ መሆን እና ከእነሱ ጋር በደስታ መኖር ይፈጥራል።

## ሐ. ሀብትን በአግባቡ መጠቀም

የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ መስፋፋት እና የኑሮ ደረጃ መጨመር የንብረት አጠቃቀም ፍላጎት እንዲጨምር አድርጓል። እነዚህን ሀብቶች አለአግባብ መጠቀም ግን አካባቢን ይጎዳል። ለምሳሌ፤ አካባቢ እንዲቆሽሽ ያደርጋል፤ የአየር ብክለት እና ከፍተኛ የአየር ሙቀት እንዲጨምር ያደርጋል።
ስለዚህ የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ መጠቀም የተፈጥሮ ሃብት እጥረትን ከመቅረፍ ባለፈ ለአካባቢው ተጽእኖ መፍትሄ ይሆናል። የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቶችን ለመጠበቅና
ለመጠቀም በጣም አስፈላጊ ነገሮች ጥቂቶቹ፡ ጊዜ፣ ገንዘብ፣ የተለያዩ ቁሳቁሶች፣ መሬት፣ ሰዎች፣ ወንዞች፣ ደኖች፣ እንስሳትና ወዘተ. ናቸው።

## ተግባር 6

1. የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሃብቶችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለብህ/ሽ? ኃላፊነት ካለብህ/ሽ ምን ማድረግ ይጠበቅብሃል/ሻል?
2. ክረምት ላይ ምን ታደርጋለህ/ጊያለሽ?
3. ቤተሰብህ/ሽ በሀብት አጠቃቀም የማቀድ ልምድ አላቸው?

### መ. በማህበረሰቡ ውስጥ በንቃት ይሳተፉ

የማህበረሰብ ተሳትፎ የማህበረሰብ ችግሮችን ለመፍታት በሚደረግ ስራ ላይ መሳተፍ ይመለከታል። ሰዎች በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ይገናኛሉ። ተማሪዎች የህብረተሰብ አካል በመሆናቸው በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ሚና አላቸው። ስለዚህ ተማሪዎች ከማህበረሰባቸው ጋር በአንድነት መስራት ይጠበቅባቸዋል። ከፍተኛ የማህበረሰብ ተሳትፎ የሚያደርጉ ተማሪዎች ጥሩ ዜጋ ይባላሉ። ይህ የሚያሳየው ማንኛውም ዜጋ በችሎታው ማህበረሰቡን ማገልገል እንዳለበት ነው። የተማሪዎች ዋና ተግባር ትምህርት በመሆኑ በትክክል ማጥናት ይጠበቅባቸዋል። ይሁን እንጂ በእረፍት ጊዜ እና በማህበራዊ ችግሮች ውስጥ በንቃት መሳተፍ አለባቸው። ለምሳሌ፤ ንቁ ተሳትፎን ከሚሹ የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ።

1. አካባቢን ማጽዳት፤
2. ለጎረቤቶች መላላክ፤
3. ችግኞችን መትከልና መንከባከብ፤
4. የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት፤
5. አድሎ አለመስራት።

## ተግባር 7

1. የነቃ ተሳትፎ ተብለው ከላይ ከተዘረዘሩት የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በየትኛው ላይ ተሳትፈሀል/ሻል?
2. የነቃ ተሳትፎ ካለህ/ሽ ለጓደኛህ/ሽ ንገር/ሪ።
3. ለወደፊቱ እንደዚህ ባሉ የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ ፈቃደኛ ነህ/ሽ?

## ሠ. ግብርን በወቅቱ መክፈል


**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

ቤተሰብዎ ግብር ይከፍላል? ለምን ግብር እንደሚከፍሉ ጠይቀህ ታውቃለህ?

ታክስ የአንድ ሀገር ዜጎች በስራቸው መሰረት ለመንግስት የሚከፍሉት ክፍያ ነው። ይህ ሁሉም ዜጎች ሊወጡት የሚገባ ኃላፊነት ነው። የግብር አከፋፈል በሁሉም የዓለም ሀገሮች ውስጥ ይሠራል። በአንድ ሀገር ዜጎች የሚከፈለው ግብር የመንግስትን ገቢ በመጨመር የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ያስፋፋል።

## ረ. የትራፊክ ህጎችን ማክበር

የትራፊክ ህጎችን ማክበር የመኪና መንገድን ስንሻገር ልንፈጽመው የሚገባ ተግባር ነው።



ምስል፡ 1.7 የትራፊክ ህጎችን ማክበር

## አንዳንድ የትራፊክ ህግ መመሪያዎች

- መንገድ ስንሻገር ግራና ቀኝ በመመልከት በዜብራ መሻገር፣
- የመኪና መንገድ በእግር ስንሄድ ግራ አቅጣጫ መያዝ፣
- መንገድ ላይ አለመጫወት፣
- በመንገድ ላይ ሲራመዱ አለመቸኮል፣
- የትራፊክ ምልክቶችን ማክበር፣
- ቀይ መብራት ሲበራ ለመኪና 'አቁም' ለእግረኞች ተሻገሩ ማለት እንደሆነ መረዳት፣
- አረንጓዴው ብርሃን ለመኪና 'ሂድ' ለእግረኞች ደግሞ ቁም ማለት እንደሆነ መረዳት፣
- ከመኪና ሲወረድ የመኪናውን በር ከመክፈት በፊት አካባቢውን መቃኘት፣
- እግረኞች አደባባይ በመዞር መንገድ አለማቋረጥ፣
- መኪና ውስጥ ሆኖ እጅን በመስኮት አለማውጣት።

### ተግባር 8

ከላይ ባሉት የትራፊክ ህጎች መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. የመኪና መንገድን በምታቋርጥበት/ጪበት ጊዜ ማክበር ያለብህ/ሽ ዋነኛ የምትለው/ዪው የትራፊክ ህግ ምንድን ነው?
2. ሌሎች ምን ዓይነት የትራፊክ ህጎችን ማክበር አለብህ/ሽ?

### ሸ. የ'ወዮማ' ህግ

ማህበራዊነትን ከሚያጠናክሩ ነገሮች መካከል አንዱ የማህበራዊ ደንቦችን ማክበር ነው። ማንኛውም ማህበረሰብ አብሮ የሚኖርባቸው ህጎች አሉት። ይህ ማለት ማንኛውም የማህበረሰብ አባል የሚሰራው እና የማይሰራው ነገር አለው ማለት ነው። ስለዚህ ከአንድ ሰው የሚጠበቅበትን ማድረግ ማለት የሕብረተሰቡን ህግ ማክበር ማለት ነው፣ ይህም ማህበራዊነትን ያጠናክራል። በሌላ በኩል ማድረግ የሌለብንን ፈጽሞ መገኘት ማህበራዊ ደንቦችን መጣስ ማለት ነው። እንደኦሮሞ የማህበረሰቡን ህግ ማክበር 'ወዮማ' ይባላል። 'ወዮማ' ለተለያዩ

አካላት ይሰጣል፡- 'ዋቃፍ ወዮማ፣ ለፋፍ ወዮማ፣ ነማፍ ወዮማ' ይባላል። ትርጉሙም ለፈጣሪ ክበር ይገባዋል፣ ለመሬት ክበር ይገበዋል፣ ለሰው ክበር ይገበዋል ማለት ነው። ፈጣሪ ክብር ነው፣ ከሰማይ የሚመጣው ሁሉ የተከበረ ነው። ፈጣሪ አይወቀስም። ስለዚህም ኦሮሞዎች "ሰፉ ዋቃፍ!" በማለት ክብሩን ለፈጣሪያቸው ይገልፃሉ።

ሰዎች በማህበራዊ መዋቅር ውስጥ ባላቸው ሚና እና በዕድሜያቸው የተከበሩ ናቸው። በማህበረሰቡ ዘንድ የተከበሩ ሰዎችን ማክብር 'የሰው ወዮማ' ብለን እንጠራዋለን። ለምሳሌ አባትና እናት  የተከበሩ ናቸው፣ ሽማግሌዎችና አባ ገዳዎች የተከበሩ ናቸው።

'አርዳ ጅላዎች' በማህበረሰቡ ወነች የሚከበሩ ቦታዎች ናቸው። ኦሮሞዎች ለ'አርዳ ጅላ' አካባቢዎች ትልቅ ክብር አላቸው። አርዳ ጅላ እንደሌሎች ቦታዎች አይቆፈርም፣ ዛፍም አይቆረጥበትም።

## ተግባር 9

1. እንደኦሮሞ ማህበረሰብ ማህበራዊ ደንቦችን ማክበር ምን ተብሎ ይታወቃል?
2. በኦሮሞ ማህበረሰብ ወዮማ የሚሰጣቸው ዋና ዋና አካላትን ዘርዝሩ።

## ማጠቃለያ

ኃላፊነት ማለት የሚጠበቁ ተግባራትን በተጠበቀው ጊዜ እና በሚጠበቀው መንገድ ማከናወን መቻል ማለት ነው። እነዚህ ድርጊቶች ስለ ጓደኞች ማሰብ፣ ስለ ቤተሰብ ማሰብ እና ስለ ጎረቤቶች ማሰብ፤ በበጎ ፈቃደኝነት ማህበረሰቡን መርዳት፣ ስህተትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅን ወዘተ ይጨምራል።

ኃላፊነትን መወጣት ማለት የሚጠበቅብንን ስራ በጥሩ ሁኔታ መስራት ማለት ነው። ሰዎች ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ሥራው በትክክል ሊሠራ አይችልም። ከዚህም በላይ የሰዎች ህይወት እንዳይሻሻል በማድረግ ችግር ይፈጥራል። የተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች አሉ። የኃላፊነት ደረጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤ የግለሰብ ደረጃ ኃላፊነት፤ የቤተሰብ ደረጃ ኃላፊነት፤ ማህበረሰብ ደረጃ ኃላፊነትና በአገር ደረጃ የሚጠበቅ ኃላፊነት ናቸው።

ሰዎች በተለያዩ ደረጃዎች የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ። ለምሳሌ ቃልን ማክበር፣ ሌሎችን መርዳት፣ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም፣ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣ በጊዜ ግብር መክፈል፣ የትራፊክ ህጎችን ማክበር፣ አካባቢን መንከባከብ እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

# የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

**ትዕዛዝ 1.** የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ።

1. ህግ መጣስ ትክክል አይደለም::
2. ውሸት ጥሩ ነው።
3. እስክሪብቶ ከሌላ ሰው ወስዶ አለመመለስ ስህተት ነው።
4. ለተቸገሩ ሰዎች መርዳት የለብንም።
5. ሰዎችን ማታለል ስህተት ነው።

**ትዕዛዝ 2፡** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከአማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ።

1. ሁሌም እውነትን መናገር ያለብህ/ሽ ለምንድነው?
   ሀ. ታማኝ ለመሆን
   ለ. በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት ለማገኘት
   ሐ. መዋሸት መጥፎ ስለሆነ
   መ. ሁሉም
2. መስረቅ የለብህም። ምክንያቱም፤
   ሀ. ታማኝነት ታጣለህ።
   ለ. ከተያዝክ ስለምትታሰር
   ሐ. መስረቅ መጥፎ ተግባር ስለሆነ
   መ. ሁሉም
3. ካለህ ላይ ለሌሎች ሰዎች መስጠት ጥሩ ነው። ምክንያቱም፤
   ሀ. እርስ በርስ መረዳዳት ጥሩ ባህል ስለሆነ
   ለ. ለሌላ ሰው ከሰጠህ እርካታ ስለምታገኝ
   ሐ. መለገስ መልካም ባህሪ ስለሆነ
   መ. ሁሉም

**ትእዛዝ 3፡** የሚከተለውን ታሪክ አንብብና/ቢና ከስሩ ያሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ።

1. ደሚቱ እና እህቷ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ትምህርት ጨርሰው ወደቤታቸው ሲመለሱ ደሚቱ ከጓደኛዋ ጋር ለጥቂት ደቂቃዎች ተጫውታ ከእህቷ በ30 ደቂቃ ዘግይታ ወደ ቤቷ ገባች።

   ሀ) የደሚቱ ኃላፊነት ምንድን ነው?

   ለ) ደሚቱ ሃላፊነቷን የተወጣች ይመስላችኋል? ለምን?

   ሐ) ደሚቱ በድርጊቷ ምክንያት መመከር ያለባት ይመስላችኋል? ምን ተብላ ትመከር?

2. ሙባረክ ከጓደኞቹ ጋር በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እግር ኳስ ይጫወታል። እናቱ 6፡00 ላይ ወደቤቱ መግባት እንዳለበት ነግራው ስለነበረ የመግቢያውን ሰአት እየተቆጣጠረ ይጫወት ነበር። 5፡00 ሲሆን ጓደኛው ለአንድ ሰአት ተጨማሪ መጫወት እንደሚፈልግ ነገረው። ሙባረክ ግን ተጨማሪ አንድ ሰአት ቢጫወት 6፡00 ላይ መግባት እንደማይችል ስለሚያውቅ ወጥቶ ወደ ቤቱ ሄደ።

   ሀ) የሙባረክ ኃላፊነት ምንድን ነው?

   ለ) ሃላፊነቱን ተወጥቷል?

   ሐ) በድርጊቱ ምክንያት መበረታታት ያለበት ይመስልሃል/ ሻል?

3. አንድ ቀን ተሊሌ በአያቷ የአትክልት ስፍራ ውስጥ ዛፍ ለመትከል ወሰነች። ተሊሌ የዛን ቀን ሄዳ ለማገዝ ብታስብም ዝናብ ስለነበረ መሄድ አልቻለችም። ይሁን እንጂ አክስቷ እርዳታ እንደሚያስፈልጋት ስለምታውቅ መቅረት ከብዷታል። በዚህ ምክንያት የዝናብ ካፖርትዋን ለብሳ አክስቷን ልትረዳ ሄደች።

   ሀ) የተሊሌ ኃላፊነት ምንድን ነው?

   ለ) ተሊሌ ሃላፊነቷን ተወጥታለች?

   ሐ) በድርጊቷ ምክንያት መበረታታት አለባት ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ?

4. አንድ ቀን ጫልቱ ከብቶችን እንድታሰማራ ታዘዘች። ከብቶቹን ዋጅማ (ስዲሳ) ሳር እንዳታስበላ ማስጠንቀቅያ ተሰጥቷት አሰማራቻቸው። ጫልቱ ግን ሳሩን ስለወደደች ከብቶቹ እንዲበሉ አደረገች። ከዚያ ከብቶቹ ብዙም ሳይቆዩ ታመው ሞቱ።

ሀ) የጫልቱ ኃላፊነት ምንድን ነው?

ለ) ጫልቱ ሃላፊነቷን ተወጥታለች?

ሐ) በድርጊቷ ምክንያት መመከር ያለባት ይመስልሃል/ ሻል?

# ምዕራፍ 2

# ጠንክሮ የመስራት ባህል

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለጠንክሮ የመስራት ባህል፣ ስለአስፈላጊነቱ እና ስለመገላጫዎቹ ትማራለህ/ሪያለሽ። እንዲሁም የማንበብ ችሎታዎችን ለማዳበር የንባብ ልምዶችን እና ስልቶችን ትቀስማለህ/ሚያለሽ።

**ቁልፍ ቃላት እና ሐረጋት፤** ጠንክሮ የመሥራት ባህል፤ የልጅ መጎሳቆል፤ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ፤ የንባብ ባህሪያት፤ የንባብ ስልቶች፤ የሙያ ክህሎቶች

## የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ጠንክሮ የመስራት ባህል ምንነትን መግለጽ፤
- የጠንክሮ መስራት ባህልን አስፈላጊነት መገንዘብ፤
- ጠንክሮ የመሥራት ባህል ያለውን ሰው ባህሪያት መዘርዘር፤
- እንዴት የራስህን/ሽን ስራ ማቀድ እንደምትችል/ዪ መለየት።

## 2.1. ጠንክሮ የመስራት ባህል ምንነት

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምርት በኋላ፡-

- የጠንክሮ መስራት ባህል ምንነትን ትገልጻለህ/ጫለሽ፤
- ጠንክሮ በመስራት ባህል ህይወታቸውን ያሻሻሉ ሰዎችን ታደንቃለህ/ቂያለሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

- ጠንክሮ የመስራት ባህል ምንድን ነው?
- በባህል እና ጠንክሮ በመስራት መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?
- ጠንክሮ መሥራት ለምን አስፈለገ?
- በህይወታችን ስኬት የሚገኘው በዕድል ነው ወይንስ ጠንክሮ በመሥራት ነው?

ሥራ የሕይወት መሠረት ነው። ውጤታማ ሥራ መሥራት የሰውን ሕይወት ያቃናል። ይህም ከጠንካራ የስራ ባህል የሚመነጭ ነው። ጠንካራ የሥራ ባህል የሚገኘው በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ተስፋ ሳይቆርጡ በርትቶ በመስራት ነው። ጠንክሮ የመስራት ባህል፣ ጉልበትን እና ጊዜን መስዋእት በማድረግ ውጤታማ ስራ በቋሚነት መስራት ነው። ይህ ደግሞ ለስራው የተሰጠውን ጊዜ ለስራው ብቻ ማዋል፣ ለስራው የተሰጠውን ቁሳቁስ አለማባከን፣ ስራን ማቀድ፣ ስራን አለመናቅ፤ በርትቶ መስራት፣ ጥሩ የውድድር መንፈስ እና አብሮ የመስራት ባህል እንዲኖረን ማድረግ ይገኙበታል።





ምስል 2.1: ጠንካራ የስራ ባህል ያላቸው ሰዎች

ሰውን ሰው የሚያደርገው ሥራ ነው። ጠንካራ ተማሪዎች መምህሮቻቸውን በቅርበት ስለሚከታተሉ እና ጠንክረው ስለሚያጠኑ በትምህርታቸው ስኬታማ ይሆናሉ። ሰዎች ጠንክረው ስለሚሠሩ ሀብታም ይሆናሉ። ይህ ደግሞ ጠንክሮ የመስራት ባህል ያለው ማንኛውም ሰው በህይወቱ ስኬታማ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል። ስለዚህ ሰዎችን ሀብታምና ድሀ የሚያደርጋቸው የጠንክሮ መስራት ባህል ባለቤት መሆናቸው ወይም አለመሆናቸው ነው። ዜጎቻቸው ጠንክሮ የመሥራት ባህል ያላቸው ሀገሮች በፍጥነት ያድጋሉ። ዜጎቻቸው ጠንክሮ የመሥራት ባህል የሌላቸው ሀገሮች ደግሞ እድገታቸው አዝጋሚ ይሆናል። ለምሳሌ ጃፓንንና ቻይናን የመሳሰሉ ሀገራት በአለም ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ካሉ ሀገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። ምክንያቱም ዜጎቻቸው ጠንክሮ የመስራት ባህል ስላላቸው ነው።



ምስል 2.2 ጠንክሮ የመስራት ባህልን ማጎልበት አስፈላጊ ነው

ጠንክሮ መሥራት ጥሩ እድሎችን ያስገኛል። ጠንክረው ሲሰሩ የተሻለ እድል ይኖራቸዋል። ውጤታማ ሆኖ ለፍሬ መብቃት ሌላ ምስጢር የለውም። ምስጢሩ ራስን ማዘጋጀት፣ ጠንክሮ መሥራት እና ከውድቀት መማር ነው። ስለዚህ ሰዎች ስኬት መታደል ነው ብለው ከሚያስቡ ይልቅ ጠንክሮ መስራትን ባህል ቢያደርጉ ተመራጭ ነው።

## ተግባር 1

1. የቤተሰብህን/ሽን አባል አንዳንድ የስራ ባህሎች ዘርዝር/ሪ።
2. በአካባቢህ/ሽ በጣም የተለመዱ የስራ ባህል መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?
3. የጠንክሮ መስራት ባህልን እንዴት ተረዳኸው/ሽው?
4. ከጠንክሮ መስራት ወይም ከዕድል በየትኛው ታምናለህ/ሽ? ለምን?

## 2.2. የጠንክሮ መስራት ባህል አስፈላጊነት

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምርት በኋላ፡-

- ጠንክሮ የመስራት ባህል ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ታስረዳለህ/ሽ፤
- ስራህ/ሽን ጠንክረህ/ሽ ትሰራለህ/ሪያለሽ፤
- ሰዎች ጠንክረው እንዲሰሩ ታበረታታለህ/ቺያለሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄ

- የ5ኛ ክፍል ተማሪ እንደመሆንህ/ሽ በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጪ ለመስራት ያሰብከው/ሽው ምንድን ነው?

እያንዳንዱ ሥራ ጠንክሮ መሥራትን ይፈልጋል። ለምሳሌ፤ ተማሪዎች ግባቸውን ለማሳካት ጠንክረው ማጥናት አለባቸው። ምክንያቱም ዛሬ ጠንክሮ መሥራት ለነገ ስኬትን ያመጣል።

ጠንክሮ የመስራት ባህልን ማዳበር ብልጽግናን ሲያመጣ ጠንክሮ የመስራት ባህልን አለማዳበር ግን ውድቀትን ያስከትላል። ከዚህ አንጻር ጠንክረው ያጠኑ ተማሪዎች ስኬታማ ሆነው ህልማቸውን ሲያሳኩ፣ ጠንክረው ያላጠኑ ተማሪዎች ግን ካሰቡት ሊደርሱ አይችሉም። ጠንክረው ያጠኑ ተማሪዎች ስኬታማ መሆን ቤተሰቦቻቸውን ያሰደስታል። ጠንክረው የማጥናት ባህል የሌላቸው ተማሪዎች ውድቀት ግን ቤተሰቦቻቸው ያሳዝናል። ስለዚህ ተማሪዎች ጠንክሮ የማጥናት ባህል እንዲያዳብሩ ይጠበቃል።

የታታሪነት ባህል ከተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ማህበረሰብ አባላት ማለትም ከነጋዴዎች፣ ከአርሶ አደሮች፣ ከአርብቶ አደሮችና ከመንግስት ሰራተኞች ይጠበቃል። ይህ ደግሞ ድህነትን ያስወግዳል፤ እንዲሁም እድገትን ያፋጥናል። በተጨማሪም የሰው ሃይል እና ሌሎች ሀብቶች በብቃት ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል። ስለሆነም ሰዎች ሁሉ ጠንክሮ መሥራትን ባህል ማድረግ አለባቸው።



ምስል 2.3፡ በርትቶ መማር ስኬታማ ያደርጋል

## ተግባር 2

1. ጠንክሮ የመሥራት አስፈላጊነት ምንድነው?
2. ጠንክሮ መሥራት አስፈላጊ ነው ብለህ/ሽ ታምናለህ/ሽ? ለምን?
3. ጠንክሮ የመስራት ባህል ማዳበር ምን ጥቅሞች አሉት?

## 2.3. የጠንካራ ተማሪ የስራ ባህል መገላጫዎች

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የጠንካራ ተማሪዎችን የሥራ ባህል መገለጫዎች ትገልጻለህ/ጫለሽ፤
- ጠንክረው የሚሰሩ ሰዎች ባህላዊ መገለጫዎችን ተግባራዊ ታደርጋለህ/ጊያለሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

- በጣም ጠንካራ ተማሪዎች እንዴት ያሉት ናቸው?
- አንተ/አንቺ ጠንካራ ተማሪ ነህ/ነሽ? በምን ይገለጻል?

ተማሪዎች ጠንካራ መሆን አለባቸው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል በትምህርት ቤት በሰዓቱ መገኘት፣ የቤት ሥራዎችን በወቅቱ በማጠናቀቅ ማቅረብ፣ በደንብ ማጥናት ወዘተ ናቸው። በተጨማሪም ጠንካራ ተሳትፎ ማድረግ፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ጥያቄዎችን በትህትና መመለስ ናቸው። እነዚህ ሁኔታዎች ተማሪዎች ጥሩ ስነምግባር እንዲያዳብሩ እና ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የሚያበረታቱ ይሆናሉ።



ምስል 2.5 በጋራ የመስራትና የማጥናት ባህልን ማጠናከር

ጠንካራ ተማሪዎች በመማር ሂደት በሚገኝ ስኬት የሚያምኑ ጥሩ ልምድ ያላቸው ናቸው። እንደዚህ አይነት ተማሪዎች ትምህርት ቤት በሚፈጥርላቸው እድሎች በመጠቀም የሚጠበቅባቸውን ተግባራት በቁርጠኝነት ይፈጽማሉ። ስለዚህ ጠንክሮ መስራት የጠንካራ ተማሪዎች ባህሪ ነው። ጠንካራ ተማሪዎች የመማር ብቃታቸውን እና ክህሎቶቻቸውን የበለጠ ለማሳደግ ይጥራሉ። ያገኙትን እውቀት፣ ችሎታ እና እውቀት ተግባራዊ ያደርጋሉ። በተጨማሪም ጠንካራ ተማሪዎች ስህተታቸውን በመቀበል ያሻሽላሉ። በትምህርት ቤትም ሆነ ከቤት ውጪ በሥራቸው ስኬታማ ይሆናሉ። ከዚህም አንጻር ሁሉም ተማሪዎች ጠንክሮ የመስራት እና ጠንክሮ የመማር ልምድ እንዲኖራቸው ይጠበቃል።

የማህበረሰብ ባህል የተማሪዎችን ደህንነትን በማረጋገጥ እና ኑሯቸውን በማሻሻል ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ተማሪዎች ጠንክረው እንዲሰሩ ማስተማር የልጆችን ጉልበት ማባከን አይደለም። ተማሪዎች ጠንክረው እንዲሰሩ ማስተማር በታማኝነት ጥሩ ስራ እንዲሰሩ ማስቻል ነው። በልበ ሙሉነት የወደፊት ህይወታቸው እንዲሳካላቸው ተማሪዎችን ጠንክረው እንዲሰሩ ማስተማር የህጻናትን ጉልበት አለአግባብ መጠቀም ሳይሆን ጠንክሮ የመስራት ባህልን

እንዲያዳብሩ ማገዝ ነው። በአጠቃላይ ጠንካራ ተማሪዎች፡-

- ሁልጊዜ በትምህርት ቤት በሰዓት ይገኛሉ፤
- ማስታወሻ ይወስዳሉ፤
- የቤት ስራን በትክክል ይሰራሉ፤
- ትምህርታቸውን በትኩረት ይከታተላሉ፣ ያልተረዱትን ጥያቄዎች ይጠይቃሉ፤
- በክበብ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፤
- ከመምህራን ጋር ጥሩ ግንኙነት ይኖራቸዋል፤
- በመማር ሂደት ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ፤
- ሁልጊዜ ጠንክረው ያጠናሉ።

### ተግባር 3

አንተ/አንቺ ጠንካራ ተማሪ ነህ/ነሽ? የጠንካራ ተማሪዎች ባህሪያት ምን ምን ናቸው?

## 2.4. የማንበብ ባህል

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የማንበብ ባህል ምን እንደሆነ ታስረዳለህ/ጃለሽ፤
- የማንበብ ባህልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶችን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- የማንበብ ባህል ታዳብራለህ/ሪያለሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

- ማንበብ ማለት ምን ማለት ነው? ከመማሪያ መጻህፍት ውጪ እስካሁን ስንት መጽሃህፍትን አንብበሃል/ሻል?
- በየቀኑ መጻህፍትን ታነባለህ/ቢያለሽ? የምታነብ/ቢ ከሆነ ምን አይነት መጻሕፍትን ማንበብ ትመርጣለህ/ጫለሽ?

"ያነበበ ሰው የሚናገረው ነገር አይጎድልበትም" የሚል አባባል አለ። ማንበብ አንባቢዎች ከጽሑፎች መረጃ የሚቀበሉበትና መረጃውን ለመገንዘብ የሚጥሩበት ሂደት ነው። በሌላ አገላለጽ ማንበብ አንባቢዎች በመጽሐፍት ውስጥ የተከማቹ እውቀቶችን እና መረጃዎችን የሚረዱበት ሂደት ነው። ማንበብ የአንድ ጊዜ ተግባር ሳይሆን ቀጣይነት ያለውና ከሰው እድገት ጋር አብሮ እየጎለበተ የሚሄድ ነው። ይህ ክህሎት በተሻለ ሁኔታ ሊጎለብት የሚችለው አንባቢዎች የሚያነቡትን የመጽሐፍ አይነት በመለየት እና ተገቢ የማንበብ ስልቶችን በመምረጥ ነው። መጻሕፍት ለተለያዩ ዓላማዎች የተጻፉ በመሆናቸው ዓላማውን መሠረት በማድረግ መነበብ አለባቸው።



ምስል 2.6፡ የማንበብ ልማድን ማጎልበት

ማንበብ ጥበበኛ ያደርጋል። እንዲሁም የህይወት ችግሮችን ለመፍታት እና ህይወትን የመምራት ብልሃቶችን ያሰገኛል። ስለዚህ የማንበብ ባህል ማዳበር ይጠበቅብናል።

የማንበብ ባህልን የሚያዳብሩ ብልሃቶች

## ሀ. በየቀኑ ለማንበብ ማቀድ

ለማንበብ የሚወስድብን ጊዜ ምናልባት ከ5-10 ደቂቃ የሚፈጅ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ቢያንስ በቀን አንዴ የመጽሐፍ ገጾችን መግለጥ ይኖርብናል፡፡ የማንበብ ልማዳችንን ዘላቂ ለማድረግ ማንበባችንን ከሌሎች የየዕለት ተግባሮቻችን ጋር እንዲዛመድ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ፣ ከተጫወትን በኋላ ወይም ሻይ ቡና በምንጠጣበት ወቅት ማንበብ፡፡ ከመተኛት በፊት ማንበብም ሌላው የማንበብ ባህልን የምናዳብርበት ጠቃሚ መንገድ ነው። እነዚህን ተግባራት ስንከውን ማንበብንም አብረን የምንከውን ከሆነ አዕምሯችን ተግባሩን እያቀናጀ ስለሚቀበለው ማንበብን ልማድ ያደርገዋል።

## ለ. ተጨማሪ መጻሕፍትን ማንበብ

ተማሪዎች የመማሪያ መጻሕፍትን ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ መጻሕፍትንም ማንበብ አለባቸው። ይህ የሚደረገው በእረፍት ጊዜ የሚፈጽሙት እና ከመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚያገኙትን እውቀት እንዲያጠናክሩ ይረዳቸዋል። ስለዚህ ለተማሪዎች የትምህርት ደረጃ እና ዕድሜ ተስማሚ የሆኑ ተጨማሪ ማራኪ መጻሕፍትን በመምረጥ ማንበብ አስፈላጊ ነው። እንደዚህ አይነት መጻሕፍትን ለመምረጥ ከከበደን የጓደኞቻችንን፣ የቤተሰብ አባላትን እና የመምህሮቻችንን እገዛ መጠየቅ እንችላለን።

## ሐ. በምንሄድበት ሥፍራ ሁሉ መጽሐፍ መያዝ

ይህ የዕረፍት ጊዜ ሲኖር ለማንበብ ይረዳሃል/ሻል።

## መ. በንበብ ክበብ ውስጥ መሳተፍ

የትምህርት ቤቱ የንባብ ክበብ አባል መሆን የማንበብ ልማድ እንድናዳብር ይረዳናል። ማንበብ ግንዛቤያችንን እና ልምዳችንን የበለጠ እንድናሳድግ

የሚያስችል ተግባራችን መሆን አለበት። የማንበብ ባህል ካለን በትምህርት ውጤታችን እና በማህበራዊ ህይወታችን ስኬታማ እንሆናለን። ስለዚህ መጻሕፍትን የማንበብ ባህል ማዳበራችን ኑሯችንን በእውቀት እንድንመራ ያስችላል፤ ስልጡንም ያደርገናል።

ነገር ግን የማንበብ ባህል ከሌለን እውቀታችን እና ልምዳችን ውስን ይሆናሉ። በዚህም ምክንያት የቤት ስራችንን እና ፈተናችንን ከጓደኞቻችን ኮርጀን ለመምህሮቻችን ለማሳየት እንሞክራለን። ይህ ደግሞ መዋሸት እና የማይገባንን በአቋራጭ መንገድ ለማግኘት መጣር ነው። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ሥነምግባር (ግብረገብነት) የጎደለው ድርጊት ነው። ሥነ ምግባር (ግብረገብነት) መጣሳችን ደግሞ በጠንካራ ተማሪዎች፣ በመምህራን እና በህብረተሰቡ ውስጥ የተወገዘን ያደርገናል። ስለዚህ ተማሪዎች ሁሉ የማንበብ እና የስራ ባህልን ማዳበር ይገባቸዋል።

### ተግባር 4

1. የንባብ ባህልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶች ምን ምን ናቸው?
2. የማንበብ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?
3. ገና በልጅነት የንባብ ባህል እንዴት ማዳበር ይቻላል?

## 2.5. የንባብ ባህልን የሚያዳብሩ ብልሃቶች

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የማንበብ ክህሎትን የሚያዳብሩ ብልሃቶችን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- ውጤታማ በሆነ መንገድ ማንበብ እንዴት እንደሚቻል ትለያለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄ

- የማንበብ ችሎታን የሚያዳብሩ ብልሃቶችን መዘርዘር ትችላለህ/ያለሽ?

የማንበብ ክህሎት የሚዳበረው በተለያዩ ብልሃቶች ነው። የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችን መጠቀም ተማሪዎችን በብቃት እንዲያነቡ ይረዳል። የማንበብ ክህሎትን ከሚያዳብሩ አንዳንድ ብልሃቶች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

### ሀ. ለዓላማ ማንበብ

ተማሪዎች ለተለያዩ ዓላማዎች መጻሕፍትን ያነባሉ። ከነሱ መካከል ዋናው የክፍል ትምህርት ይዘትን በደንብ ለመረዳት ማንበብ ነው። እንዲህ ያለ ንባብ የክፍል ስራን፣ የቤት ስራን፣ መለማመጃዎችን እና ፈተናዎችን ለመስራት ያግዛል። እንዲሁም በዕረፍት ጊዜ የሚነበቡ መጻሕፍት የተማሪዎችን እውቀት ለማጠናከር ይረዳሉ።

### ለ. መረጃ ሰጪ ቃላት ላይ በማተኮር ማንበብ

በጽሁፍ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ቃላት መረጃ ሰጪ ናቸው። ሌሎች ደግሞ እርስበርስ የማጣማር እና የማንበብ ፍላጎትን ለማነሳሳት ያገለግላሉ። ስለዚህ የጽሑፉን ይዘት መረጃ ወይም ትርጉም የሚሸከሙትን ቃላት በትኩረት ማንበብ አስፈላጊ ነው። ይህም የማንበብ ግንዛቤን እና ፍጥነትን ይጨምራል። ተማሪዎች ከጽሑፉ ውስጥ እንዲረዱት በሚፈልጉት ጉዳይ ላይ በማተኮር በማንበብ የመረጃ ቃላትን መለየት ይችላሉ።

### ሐ. ማስታወሻ መያዝ

ማስታወሻ በመያዝ ማንበብ ተማሪዎች ማዳበር ያለባቸው የማንበብ ብልሃት ነው። ምክንያቱም ባነበቡት ጽሁፍ ጥልቅ ግንዛቤ ለማግኘትና ዝርዝር ማብራሪያ ለመስጠት የሚረዱ ነጥቦችን ለማግኘት ይረዳቸዋል። በተጨማሪም ማስታወሻ መያዝ በፍጥነት እንዲያስታውሱ እና ለፈተና እንዲዘጋጁ ያግዛቸዋል። ስለዚህ የማንበብ ባህልን ለማዳበር ማስታወሻ መያዝ ሁሉም ተማሪዎች ሊያገኙት የሚገባ የማንበብ ብልሃት ነው።

ማንበብን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ፡-

- ለማንበብ በቂ ብርሃን እና ጸጥታ ያለው ቦታ መምረጥ። በመኝታ ክፍል ውስጥ አለማንበብ፤

- ጮክ ብሎ ማንበብን ማስወገድ፤
- በዕረፍት ጊዜ እና በምቹ ቦታ ማንበብ፤
- ምን እንደሚነበብ እና የሚነበብ ይዘትን መወሰን፤
- ለማንበብ በቂ ጊዜ እንዳለ ማረጋገጥ፤

## ተግባር 5

1. የማንበብ ባህልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶች ምንድን ናቸው?
2. ማንበብን ውጤታማ ለማድረግ ምን ማድረግ አለብን?

## ማጠቃለያ

የጠንክሮ መስራት ባህልን ማጎልበት ዜጎች ከድህነት አረንቋ ወጥተው ፈጣን እድገት ለማስመዝገብ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም ሀብትና የሰው ሀይል በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ያረጋግጣል። ይህ ደግሞ በእያንዳንዱ የሥራ ቦታ አስፈላጊ ነው። ተማሪዎች ከእድሜያቸው ጋር የሚስማማ ስራ እንዲሰሩ እና ጠንክረው እንዲማሩ ይጠበቅባቸዋል። ጠንካራ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ የሚያደርጋቸውን መንገድ መከተል አለባቸው። ይህም አሁን የሚጠበቅባቸውን በማድረግ ለወደፊት ሕይወታቸው እንዲዘጋጁ ያስችላቸዋል። ስለዚህ ጠንክሮ የመስራትና የማንበብ ባህል መኖሩ በጣም አስፈላጊ ነው።

# የምዕራፍ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ትዕዛዝ I:** የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ 'እውነት' ትክክል ካልሆኑ 'ሐሰት' በማለት መልስ/ሺ።

1. የጠንክሮ መስራት ባህል ማዳበር ከሁሉም ሰው ይጠበቃል።
2. ጠንክረው የሚሰሩ ሰዎች ስኬታማ መሆን ይችላሉ።
3. ጠንክሮ መስራት በብዙ ማህበረሰብ ዘንድ ነውር ነው።
4. በአንድ ጽሁፍ ንባብ ውስጥ የሚገኙ ቃላት ከመረጃ ሰጪነት አንፃር ይበላለጣሉ።
5. የማንበብ ባህል ማዳበር ክህሎትንና እውቀትን ይቀንሳል።

**ትዕዛዝ II:** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ።

1. የጠንክሮ መስራት ባህል ማዳበር_________።
   - ሀ. ድሀ ያደርጋል
   - ለ. ድህነትን በመቀነስ በፍጥነት እንዲያድጉ ያደርጋል
   - ሐ. ብቁ እና ውጤታማ ያደርጋል
   - መ. 'ለ' እና 'ሐ' መልሶች ናቸው።
2. ከሚከተሉት ውስጥ የሰነፍ ተማሪ ባህሪ የትኛው ነው?
   - ሀ. በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፤
   - ለ. በማንበብ ተግባር ስልቹ መሆን
   - ሐ. ትምህርትን በትኩረት መከታተል፤
   - መ. የቤት ስራን በአግባቡ መስራት፤

3. የማንበብ ልምድን ስለማዳበር ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው የተሳሳተ ነው?

ሀ. በየቀኑ ለማንበብ ጊዜ መስጠት፤

ለ. መጻሕፍትን በየቦታው ይዞ መሄድ፤

ሐ. ጮክ ብሎ ማንበብ፤

መ. ተጨማሪ ጠቃሚ መጽሐፍትን ማንበብ፤

4. ህጻናት ከልጅነታቸው ጀምሮ የስራ ባህልን የሚማሩ ከሆነ፡-

ሀ. ዘላቂ የሥራ ልምድን ይጎናፀፋሉ።

ለ. ለጉልበት ብዝበዛ እንዲጋለጡ ያደርጋል።

ሐ. የልጆችን ጤና ይጎዳል።

መ. ለስራ ያላቸውን ፍላጎት ያሳጣል።

**ትዕዛዝ III: ባዶ ቦታዎችን ሙላ/ዪ።**

1. ለአንድ የተወሰነ ስራ የራስ ጊዜንና አቅምን በዘላቂነት መስዋዕት በማድረግ ጥቅም ላይ ማዋል __________ ይባላል።

2. የንባብ ባህልን ለማጠናከር የሚረዱ ብልሃቶች ________________፣ ________________ እና ________________ ናቸው፡፡

**ትዕዛዝ IV፡ ባጭሩ መልስ/ሺ።**

ልጆችን የሥራ ባህል እንዲያዳብሩ ማስተማር የልጆችን ጉልበት እንደማባከን ይቆጠራል? ለምን?

# ምዕራፍ 3

# ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ችሎታ

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በአምስት የትምህርት ክፍሎች ተከፍሎ የቀረበ ሲሆን ትክክለኛ ውሳኔዎች የመስጠት ችሎታን ያስተምራል። የዚህ ምዕራፍ ንኡሳን ይዘቶች ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ፅንሰ ሃሳብ፣ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ባህሪያት፣ የትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ቅደም ተከተል፣ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነት እና ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት እንቅፋቶች ናቸው።

ተማሪዎች በየቀኑ የተለያዩ ውሳኔዎችን ይወስናሉ። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የሚወስናቸውን ውሳኔዎችና የሚወስዷቸውን እርምጃዎች በጥንቃቄ ላያጤኑ ይችላሉ። ስለዚህ መጀመሪያ ችግር መለየትን፣ ሃሳብ ማፍለቅን እና ጥቅምንና ጉዳትን መተንተንን የመሳሰሉ ክህሎቶችን ማዳበር አለባቸው። ከዚያም በምርጫቸው መሰረት ውሳኔያቸውን መተግበር አለባቸው።

**ቁልፍ ቃላት/ሐረጋት፡-** ስነምግባር፣ ፍርድ፣ ግምገማ፣ ችግር፣ ትክክል፣ የተሻለ ምርጫ፣ ፍትህ፣ ጉዳት፣ መዘዞች

## የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-


- የውሳኔ ሃሳቦችን መረዳት፤
- ትክክለኛ ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታ ባህሪያትን መዘርዘር፤
- ምክንያታዊ ለሆኑ ውሳኔዎች ትኩረት መስጠት፤
- ትክክለኛ የውሳኔ አሰጣጥ ቅደም ተከተሎች እንዴት እንደሚተገበሩ ማሳየት፤
- ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለማድረግ እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን መለየት።

# 3.1. የትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ጽንሰ ሃሳብ

## ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ውሳኔ የሚለውን ቃል ምንነት ትገልጻለህ/ጪለሽ፤
- ትክክለኛው ውሳኔ የመስጠት ጥቅሞችን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- ትክክለኛ ውሳኔ አለማድረግ የሚያስከትለውን መዘዝ ትለያለህ/ሽ።



ምስል 3.1፡ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አስቦ መወሰን

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

- ከምስል 3.1 ምን ተገነዘብክ/ሽ?
- የተገነዘብከውን/ሽውን ጽፈህ/ሽ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ አንብብላቸው/ቢላቸው።

ልናዳብራቸው ከሚገቡን ቁልፍ ክህሎቶች መካከል ዋነኞቹ ውሳኔ የመስጠት ክህሎቶች ናቸው፡፡ ውሳኔ መስጠት ከቀረቡት አማራጮች በጣም የተሻለውን በመምረጥ ወይም በመቀበል የመጨረሻ መደምደሚያ ላይ የመድረስ ሂደት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ እኛ የምንሰጠው ውሳኔ በአእምሮ ጤንነታችን እና ደስታችን ላይ ተጽዕኖ አለው። ተግባቦታችን እና ስኬታችን በአብዛኛው በጥንቃቄ በምንወስዳቸው ትክክለኛ ውሳኔዎች ላይ ይመሰረታሉ። በሌላ በኩል፣ ትክክለኛ ውሳኔዎችን የመስጠት ችሎታ ኃላፊነት የሚሰማው እና ገለልተኛ ሰው እንድንሆን ይረዳናል።

ትክክለኛ ውሳኔዎችን የመስጠት ችሎታ፣ ግባችንን ለማሳካት እድል ይሰጠናል። ይህም በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ ውስጥ በተማርነው መሰረት የህይወታችንን አካሄድ እንድንወስን ይረዳናል። ያኔ ትክክለኛ ውሳኔ በመስጠት ከተሳካላቸው ሰዎች መካከል በመቆጠር ለማህበረሰቡ ምሳሌ መሆን እንችላለን።

ሰዎች በትክክል ከተረዱ እና ለግለሰብ፣ ለቤተሰብ እና ለህብረተሰብ ጥቅም ሀላፊነት ከወሰዱ የተማሩ ሰዎች ብለን ልንጠራቸው እንችላለን።

ተግባር 1

ከቤተሰብህ/ሽ ጋር በተጨናነቀ መንገድ ላይ በእግር በምትጓዙበት ወቅት አንዲት ሴት አዛውንት አጠገብህ/ሽ ካለ የሕንፃ ደረጃ ሲወርዱ ተመለከትህ/ሽ፡፡ በድንገትም አዛውንቷ ደረጃው አደናቅፏቸው ወደቁ። ወዲያውም የመጎዳት ድምጽ አሰሙ፡፡ አንተ/አንቺ በዚህን ጊዜ ምን ዓይነት እርምጃ ልትወስድ/ጂ ትችላለህ/ያለሽ?

ሀ. የምትወስደውን/ጂውን እርምጃ ግለጽ/ጪ።

________________________________________

________________

ለ. ውሳኔህ/ሽ ትክክል ነበር? ለምን?

________________________________________

________________

## 3.2. ትክክልኛ ውሳኔ የመስጠት ችሎታ ባህሪያት

**ቢያንስ ልትጎናጸፉቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ችሎታ ጥቅሞችን ትለያለህ/ሽ፤
- ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ችሎታን ባህሪያት ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ።

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

- ከዚህ ቀደም በማንኛውም ጉዳይ የሰጠኸውን/ሽውን ውሳኔ ለጓደኞችህ/ሽ አጋራ/ሪ።
- ውሳኔው ትክክል ወይም ስህተት ነበር? ለምን?

ትክክለኛውን ውሳኔ መስጠት ማለት ከተመረጡት አማራጮች መካከል በጣም ሚዛናዊውን እና የተሻለውን የውሳኔ ሂደት መምረጥ ማለት ነው። ውሳኔ በምንሰጥበት ጊዜ ለሚመለከታቸው ሁሉ ጥሩ ውጤት ካመጣ ትክክለኛ ወይም ጥሩ ውሳኔ ነው እንላለን። ትክክለኛውን ውሳኔ በማድረግ ሂደት ውስጥ፤ ጥሩ እና መጥፎ ምርጫዎችን ለመገምገም የሰው አእምሮ በተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ መሆን አለበት። ለአንድ የተለየ ሁኔታ የትኛው አማራጭ ተስማሚ እንደሆነ መወሰን ያስፈልጋል። ትክክለኛ ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታ የሚከተሉት ባህሪያት አሉት።

## 1. ማሰብ/ማሰላሰል

ውሳኔ የመስጠት ክህሎት፣ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ አማራጮች መካከል ይበልጥ ተቀባይነት ያለውንና ትክክለኛውን የመውሰድ ችሎታ ነው። ያሉትን መረጃዎች በሙሉ ከገመገመክ/ሽ በኋላ ምክንያታዊውንና ትክክለኛውን ውሳኔ መስጠት ትችላለህ/ያለሽ።

## 2. ምክንያታዊነት

ምክንያታዊነት ማለት አሳማኝ እና እውነተኛ ወይም ተጨባጭ ሀሳብ ማቅረብ ነው። በተጨማሪም ችግርን የመለየት ሂደቶችን እና መፍትሄዎችን ያካትታል። ችግርን መለየት በውሳኔዎቻችን ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩትን ነገሮች ማወቅ እና መፍትሄ መፈለግን ያካትታል። ምክንያታዊነት በጣም አስፈላጊ ከሆኑ የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታዎች አንዱ ነው። ውሳኔ በምናደርግበት ጊዜ እርምጃ ለመውሰድ ያለውን ጥቅምና ጉዳት ግምት ውስጥ ማስገባት አለብን። ይህንን ማድረግ ከቻልን አሁን ስላሉት ችግሮች ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለማድረግ እና ለወደፊቱ እቅድ ለማውጣት ይረዳናል።

## 3. ሚዛናዊ ውሳኔ መስጠት

### የጉዳይ ጥናት

በአንድ ወቅት ጅብና አንበሳ አብረው ይኖሩ ነበር። ጅብ አንድ ላም ነበረው። አንበሳው ደግሞ ሰንጋ ነበረው። ተራ በተራ ከብቶቻቸውን አብረው እየጠበቁ ይኖሩ ነበር። የአንበሳ የጥበቃ ተራ በደረሰ ጊዜ የጅቡ ላም ወለደች። አንበሳው "ልክ እንደገባሁ፣ ይኸው የኔ ሰንጋ ጥጃ ወለደልኝ!" ብሎ ለጅቡ ነገረው። ጅቡ ነገሩ ግራ ስለገባው "ላሜ ካልሆነች ያንተ ሰንጋ እንዴት ይወልዳል?" አለ። አንበሳው ግን "ሰንጋዬ ነው የወለደው" በማለት አጥብቆ ተከራከረ። ይህን ጉዳይ ሽማግሌ እንዲያይ ተስማምተው የዱር እንስሳትን ሁሉ በጥዋት አስጠሩ። ከጦጢት በስተቀር ሁሉም እንስሳት ጠዋት በአንበሳ ቤት ውስጥ ተሰበሰቡ። እንስሳቱ የጅብና አንበሳን ሃሳብ ከተቀበሉ በኋላ ሁሉም "የአንበሳ ሰንጋ ነው የወለደው!" ብለው ወሰኑ።

ይሁን እንጂ ጦጢት አርፍዳ መጣች። ከዚያም አንበሳው፣ “ጦጢት፣ ለምን አረፈድሽ?” ብሎ ተቆጣት። እሷም፣ ዛፉ ላይ ወጥታ፣ “ይቅርታ! መሬት ተሰንጥቆ ስሰፋ ነው ያረፈድኩት” አለች። አንበሳውም በምላሿ በመናደድ፣ “ ከመቼ ወዲህ ነው ምድር ተሰንጥቃ የምትሰፋው?” አላት። ጦጢትም “ሰንጋስ ከመች ወዲህ ነው ወልዶ የሚያውቀው?!” ብላ መለሰችለት። በፍርዱ የተናደደው አንበሳም ጦጢትን ለመያዝ ዛፍ ላይ ለመውጣት ሲሞክር ከዛፉ ወድቆ የጀርባ ጉዳት ደረሰበት። የተሳሳተ ፍርድ ሰጥተው የነበሩት እንስሶችም ጦጢት ለእውነት ያላትን አቋም እና ጽናት አደነቁ። በመጨረሻም አንበሳውን ፈርተው እውነትን በማጣመማቸው ተጸጽተው ጅቡን ይቅርታ ጠየቁት።

## ተግባር 2

1. ከላይ በቀረበው ተረት ውስጥ ስንት ዓይነት ውሳኔዎች ተሰጡ?
2. ሽምግልና የተቀመጡ እንስሳት ለፍርዳቸው መነሻ የሆናቸው ምን ነበር?
3. አንተ/ቺ ብትሆን/ኚ ምን ውሳኔ ትሰጥ/ጪ ነበር? ለምን?
4. በተረቱ ውስጥ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩ ጉዳዮችን ዘርዝር/ሪ።

## 3.3. ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ልንከተላቸው የሚገቡ ደረጃዎች

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ትክክለኛ የውሳኔ ቅደም ተከተልን ትዘረዝረዘለህ/ሪያለሽ።
- ሂደቱን ያልጠበቀ ውሳኔ የሚያስከትለውን ጉዳት ትለያለህ/ሽ፤

የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መሰረታዊ ቅደም ተከተሎች ችግር መለየትን፣ መረጃ መሰብሰብን እና መፍትሄ መስጠትን ያካትታሉ። ትክክለኛውን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ደረጃዎች ከተከተልን ውሳኔያችን ጥንቃቄ የተሞላበትና እና ተገቢ ይሆናል። ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በአምስት ደረጃዎች ውስጥ ማለፍ አለብን።

### ደረጃ 1: ችግርን መለየት

በትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውሰጥ የመጀመሪያው ደረጃ ችግርን መለየት ነው። ለችግሮች መለያ በጣም አጋዥ ከሆኑ ዘዴዎች አንዱ ችግሩን ለመለየት ጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው። በኋላ የተሰበሰበውን መረጃ በቀላል መንገድ ማጣራት ነው። ይህ ደግሞ የችግሩን ስር ለይቶ በችግሩ እና በምክንያቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በማሰላሰል ትክክለኛውን ውሳኔ ለማድረግ ይረዳል።

### ደረጃ 1: ችግርን መለየት

- ምን አይነት ችግር ለመለየት እየሞከርክ/ሽ ነው?
- በጣም ጥሩውን አማራጭ ለመምረጥ ችግሩ ምን እንደሆነ በትክክል ማወቅ ያስፈልግሃል/ሻል።
- ችግሩን ከለየህ/ሽ በኋላ ችግሩን ለመፍታት የሚረዱ ዘዴዎችን ማሰብ መጀመር ትችላለህ/ሽ።



ምስል 3.2፡ የቤት ስራቸውን በወቅቱ ያልሰሩ ተማሪዎች አሁን ምን ይሻለኛል? ወይኔ ጉዴ! ጊዜዬን በአግባቡ አለመጠቀሜ ጎዳኝ!...

### ተግባር 3

ሰዓት አልፎባቸው ቁርሳቸውን ገና ያልበሉ ወዲህ እና ወዲያ የሚባዝኑ ተማሪዎች አሉ። የእነዚህ ተማሪዎች ችግር ምንጭ ምንድን ነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያለሽ?

## ደረጃ 2፡ የተሻለ አማራጭ መምረጥ

ከግምት ልናስገባቸው የምንችላቸውን አማራጮች በሙሉ ከግምት በማስገባት እንዘርዝራቸው፡፡ አማራጮቻችንን መዝኖ ለመለየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንሳት እንጠይቅ አማራጫችን፡-

- መልካምነት ይጎድለዋል?
- ጎጂ ነው?
- ኢፍትሃዊ ነው?
- ሌሎችን ያስቀይማል?
- ከግባችን ጋር ተስማሚ ነው?

አንዳንድ ጊዜ የተሻሉ አማራጮችን ለይቶ ለመጠቀም ተጨማሪ መረጃ ማግኘት

ይገባን ይሆናል። ስለሆነም፡-

- ☞ ስለ ችግሩ የበለጠ ለማወቅ እንሞክር፤
- ☞ ሚስጥረኛ ከሆኑን የቤተሰብ አባላት ምክር እንጠይቅ፤
- ☞ ከመጻሕፍት፣ ከድረ ገጽ ወይም ከሌሎች ምንጮች መረጃ እንፈልግ፤
- ☞ ለእኛ ወሳኝ ስለሆነው ነገር ብቻ እናስብ፤
- ☞ ሌሎች ስለችግሩ ምን እንደሚሰማቸው እናስብ።

መረጃውን በመሰብሰብ ወቅትም ምናልባት ሌሎች አማራጮችንም ልናገኝ ወይም የፈጠራ አቅማችንን በመጠቀም አዳዲስ አማራጮችን ልንፈጥር እንችላለን፡፡ ተገቢውንና ትክክለኛውን ውሳኔ ለመወሰንም ያገኘናቸውን መረጃዎች በሙሉ መዘርዘር ይኖርብናል።

## ደረጃ 3፡ ሊደርስ የሚችለውን ውጤት መለየት

ሁለቱንም ሊደርሱ የሚችሉ አዎንታዊ እና አሉታዊ ውጤቶችን መዘርዘር ይኖርብናል። የምንወስነው እያንዳንዱ ውሳኔ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ሊኖረው ይችላል፤ ይሁን እንጂ እጅግ የተሻለው የሚባለው ለእኛ ይጠቅመናል ብለን የወሰነው ይሆናል። ጥሩ ወይም መጥፎ በሚል አማራጮችን መለየት ጠቃሚ ነው። እንደተማሪ በራሳችን በምንወስናቸው ውሳኔዎች እና በሌሎች እገዛ ልንወስናቸው በምንችላቸው ውሳኔዎች መካከል ያለውን ልዩነት ልናውቅ ይገባናል፡፡ ይህም ውሳኔ ላይ ከመድረስ በፊት ውሳኔው የሚያስከትለውን ውጤት ለማጤን ይረዳል።

የምንሰጠው ውሳኔ ያሉትን ጥቅሞችና ጉዳቶች ለመለየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንጠይቅ፡-

1. አማራጩ ጎጂ ነው ወይስ ጠቃሚ?
2. ምርጫው እንዴት ይጎዳኛል?
3. ምርጫው በሌሎች ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ያሳርፋል?
4. ይህ ምርጫ ከእሴቶቹ ጋር የሚሄድ ነው?
5. አማራጮቹ ግቦቼን እንዴት ሊጎዱቸው ይችላሉ?
6. ውሳኔው ህጉን የተከተለ ነው?

## ደረጃ 4፡ ውሳኔ መወሰንና እና ማስፈጸም

ሁሉንም መረጃዎቻችንን መዝነንና አጣርተን ከጨረስን በኋላ፣ ለኛ እጅግ የተሻ የምንለውን አማራጭ ለመምረጥ ዝግጁ እንሆናለን። አንዳንዴም ከአንድ በላይ አማራጮችን እያቀናጀን ልንጠቀም የምንችልበት አጋጣሚም ሊኖር ይችላል። በደረጃ አራት የደረስንበት ምርጫችን በደረጃ ሁለት መጨረሻ ላይ ካዘጋጀነው ዝርዝር ቀዳሚ አማራጭ ጋር አንድ አይነት ወይም የሚመሳሰልም ሊሆን ይችላል።

## ደረጃ 5፡ ውሳኔን መከለስ/ ውጤቱን መገምገም

መጨረሻ በሆነው በዚህ ደረጃ ውሳኔያችን ያስገኘው ውጤት በማጤን በደረጃ 1 ያስቀመጥነውን ፍላጎታችንን ማሟላት አለማሟላቱን እንመዝናለን። ውሳኔያችን የተፈለገውን ግብ ያላሳካ ከሆነ ሌላ አዲስ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የተወሰኑ ደረጃዎችን እንደገና ደግመን ልንፈጽማቸው ይገባናል። ለምሳሌ ሌላ ዘርዘር ያለ ወይም ከቀድሞው የተለየ መረጃ ልንሰበስብ ወይም ሌሎች ያልሞከርናቸውን አማራጮች ልንቃኝ እንችላለን፡፡ ውሳኔያችንን በምንገመግምበት ወቅት ተከታዮቹን ጥያቄዎች እናነሳለን፡-

1. የወሰንኩት ውሳኔ ምን ነበር?
2. የወሰንኩትን ውሳኔ ለምን ነበር የወሰንኩት?
3. ውሳኔዬ ለውጥ አምጥቷል ማለት ይቻላል? ለምን?
4. ይህ ውሳኔ ደህንነቴን እንዴት ሊጎዳው ቻለ?
5. ይህን ውሳኔ ደግሜ ልወስነው እችል ይሆን?

## ተግባር 4

የጉዳይ ጥናት፡ ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን

ታደሰ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነው። አንድ ቀን ብዕሩ ስለጠፋበት ወላጆቹን ገንዘብ ጠየቀ። ወላጆቹም ሰጡት። ገንዘቡን ተቀብሎ ከጓደኛው ግርማ ጋር

ወደ ትምህርት ቤት በሚሄዱበት ወቅትም በአቅራቢያቸው ከሚገኝ ሱቅ ውስጥ ብስኩቶችን ተመለከቱ። ታደሰ ገንዘብ መያዙን ግርማ ስላወቀም ብስኩት እንዲገዙ ጠየቀው። ታደሰ ብስኩቱን ቢገዛ መጻፊያ ብዕር ላይኖረው ነው፤ በተጨማሪም ቤተሰቦቹ በጣም ያዝኑበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ጓደኛው ግርማ ጋርም መቀያየም አልፈለገም፡፡

1. ግርማ ጓደኛውን ምን ጠየቀው? ጥያቄው ልክ ነበር ትላላችሁ?
2. ታደሰ ምን አደረገ?
3. እናንተ ታደሰን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

## የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

### ደረጃ 1: የሚወሰነውን ውሳኔ መለየት

1. ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚፈለገውን ሁኔታ ግለጽ/ጪ።

_______________________________________________

2. የሚመወሰነው ውሳኔ ምንድን ነው?

_______________________________________________

3. ይህ ውሳኔ ለእኔና ለጤናዬ ለምን አስፈላጊ ይሆናል?

_______________________________________________

4. ይህ ሁኔታ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን እንድከተል ያደርገኛል? /'አዎ' ወይም 'አይ'/ አስረዳ/ጂ።

_______________________________________________

5. ይህንን ውሳኔ ብቻዬን ልወስነው? ወይስ የሌሎች ሰዎችን እገዛ ልጠይቅ? ግለጽ/ጪ።

_______________________________________________

6. ይህ ውሳኔ በቀሪው ሕይወቴ ላይ ምን ተጽዕኖ ይኖረዋል?

______________________________________________________________________

____________

## ደረጃ 2፡ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን ማጤን

## ደረጃ 3፡ ሊከተሉ የሚችሉ ውጤቶችን መለየት

ምርጫህ/ሽ የውሳኔህ/ሽ ውጤት በውሳኔህ/ሽ ውጤት ሊመጣ የሚችል ጉዳት

1. ____________ ______________________ ______________________

2. ____________ ______________________ ______________________

3. ____________ ______________________ ______________________

## ደረጃ 4: ውሳኔ መስጠት እና መተግበር

ከታች ያሉትን መመዘኛዎች በመመልከት ስለ ምርጫህ/ሽ እያንዳንዱን ጥያቄ መልሽ/ሽ። 'አይ' የሚል ምላሽ የተሰጠባቸው ጥያቄዎች ካሉ አማራጩን እንደገና መፈተሽ ይገባል።

1. አማራጩ ተገቢ ነው? (አዎ/ አይ)
2. ይህ ውሳኔ ከእኔ ጋር ይሄዳል? (አዎ/ አይ)
3. ይህ ውሳኔ የእኔ የምላቸውን ሰዎች አያስቀይምም? (አዎ/ አይ)
4. ይህ አማራጭ ግቦቼን የሚያሳካ ነው? (አዎ/ አይ)
5. ይህ ውሳኔ ህጋዊነትን የተከተለ ነው? (አዎ /አይ)

## ደረጃ 5፡ ውሳኔውን መተንተንና / ውጤቱን መገምገም

### የውሳኔ መግለጫ መስጠት

የወሰንከውን/ሽውን ውሳኔ እና እንዴት ውሳኔውን እንደሰጠህ/ሽ የሚገልጽ አንቀፅ ጽፈህ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ አካፍል/ዪ። በአንቀጽህ/ሽ ውስጥ ለሚከተሉት ጥያቄዎች የተሰጡትን የተወሰኑ መልሶች ተጠቀም/ሚ።

1. የወሰንኩትን ውሳኔ ለምን ወሰንኩ?
2. የወሰንኩት ውሳኔ ለውጥ አምጥቷል? እንዴት? ካላመጣ ለምን?
3. ይህ ውሳኔ በጤንነቴ ላይ ምን ተጽዕኖ ይኖረዋል?
4. ይህንን ውሳኔ በሌላ ጊዜ ልደግመው እችል ይሆን?


## 3.4. የትክክለኛ ወሳኔ አስፈላጊነት


### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ትክክለኛ ውሳኔ አለማድረግ የሚያስከትለውን ጉዳት ትለያለህ/ሽ፤
- ትክክለኛ ውሳኔዎችን የማድረግን አስፈላጊነት ትዘርዝራለህ/ሪያለሽ።

ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት፣ በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ መማር ያለብን ጠቃሚ ችሎታ ነው። መልካም፣ ገለልተኛ እና ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ሆነን እንድናድግ ወላጆች ይፈልጋሉ። ምክንያቱም ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ከማይችሉ ሰዎች ይልቅ ትክክለኛ ውሳኔ የሚሰጡ ሰዎች ሕይወት የበለጠ ስኬታማ ነው። ስለዚህ፣ የበለጠ ራሳችንንን እየቻልን በሄድን ቁጥር ትክክለኛ ውሳኔ ማድረግን የበለጠ መማር አለብን። ተገቢ ውሳኔ የመስጠትና ችግሮችን የመፍታት ሂደትን መማርና ተግባራዊ ማድረግ ከቻልን ነገሮችን በተሻለ ሁኔታ እንፈጽማለን በህይወታችንም ስኬት እንጎናጸፋለን።





ስዕል 3.3 ነገሮችን በጉልበት ሳይሆን በብልሃት እንከውን

### ተግባር 5

ከላይ ከቀረበው ምስል ምን ተማርህ/ሽ? ከክፍል ጓደኞችህ/ሽ ጋር በጥንድ ተወያይ/ዩ። በውይይቱ ጊዜ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አገናዝብ/ቢ።

1. ውሳኔ ከማድረግህ/ሽ በፊት ስለጉዳዩ ማሰብ ያለብህ/ሽ ይመስልሃል/ሻል? ለምን?
2. አንዳንድ ውሳኔዎችን ከሌሎች የበለጠ አስፈላጊ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

ትክክለኛ ውሳኔዎችን ማድረግ በሕይወታችን ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ይህም የተሳሳቱ ውሳኔዎችን ከማድረግ እና ጉዳት ከማድረስ ይጠብቀናል። ኢ-ፍትሃዊ ወይም ሥነምግባር የጎደላቸው ውሳኔዎች ሰዎችን ይጎዳሉ። ስለዚህ ስነምግባር ያልጎደለው ውሳኔዎችን የመስጠት ችሎታ መማር በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የተሳሳቱ እና ስሜታዊ ውሳኔዎችን ከማድረግ ያድናል።

## 3.5. ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት እንቅፋቶች

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት እንቅፋቶችን ትገልጻለህ/ጫለሽ፤
- ትክክለኛ ውሳኔ ከመስጠት አንፃር እንቅፋቶቹን ማስወገድ ትችላለህ/ያለሽ።

ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ትክክለኛ ምርጫ መምረጥ መቻል ወሳኝ ነገር ነው። ይህም በተናጥል ትክክለኛ ውሳኔዎች የመስጠቱን ሂደት መረዳትን ይጠይቃል። ትክክለኛ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ግለሰቡ ከማወላወል ይልቅ በተመረጡ መንገዶች ጥሩ ውሳኔዎችን ማድረግ መቻል አለበት። አንዳንድ ሰዎች በስሜት ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ይጥራሉ፤ ነገርግን ስሜታዊ መሆን ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት እንቅፋት ነው። ትክክለኛ ውሳኔ በመስጠት ሂደት ውስጥ ሊያጋጥሙህ/ሽ የሚችሉ አንዳንድ መሰናክሎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1. **ስለራስ ያለ አመለካከት፡-** አንድ ሰው ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ሂደት ውስጥ እራሱን የሚመለከትበት መንገድ ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ላይ ተጽእኖ አለው። አንዳንድ ሰዎች ‘አውቃለሁ፤ ውሳኔዬ ሁሌም ትክክል ነው’ ይላሉ፤ መተማመናቸው ከገደቡ በላይ ነው። አንዳንድ ጊዜ በተቃራኒው በራስ የመተማመን ስሜታቸው ዝቅተኛ ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለማድረግ እንቅፋት ይሆናል

2. **ሌሎች ተጠያቂነቶች፡-** ተጠያቂነት ለአንድ ነገር፣ ሰው ወይም ሁኔታ ሀላፊነትን መውሰድ ነው። ስለሆነም ተጠያቂነትን ከመውሰዳችን በፊት በጥንቃቄ ማሰብ ያስፈልገናል፡፡ ተጠያቂነት አንድን ጉዳይ እንድንፈጽም ያስገድደናል፡፡

3. **የጓደኞች ተጽዕኖ፡-** የጓደኛ ተጽዕኖ የዕድሜ ዕኩዮች ወይም ማህበራዊ ቡድኖች ምን ይሉኛል በማለት ወይም በእነሱ ዘንድ ተወዳጅነትን ለማግኘት

ስንል አንድን ተግባር እንድንፈጽም የሚያደርገን ስሜት ነው።

4. **የቤተሰብ ፍላጎቶች፡-** ቤተሰቦች ከልጆቻቸው የሚጠብቋቸው ነገሮች አሏቸው። ልጆችም ቤተሰቦቻቸው ከእነሱ ምን እንደሚጠብቁ ያውቃሉ። ሆኖም፣ በሚሰጡት ውሳኔ ቤተሰባቸው ከነሱ ምን እንደሚጠብቅ ይጨነቃሉ። ይህ ደግሞ ትክክለኛውን ውሳኔ እንዳይሰጡ እንቅፋት ይሆንባቸዋል።

5. **የህብረተሰብ ተጽዕኖ፡-** ማንም ሰው ብቻውን አይኖርም። የሚኖረው ከማህበረሰቡ ጋር ነው። በማህበር አብሮ የመኖር ምሰሶ ደግሞ የማህበረሰቡ የስነምግባር እሴት ነው። ይህም የማህበረሰቡን አብሮ የመኖር ዕሴት እንዲጠብቅ ያስገድዳል። በዚህ ምክንያት ውሳኔን በሚጠይቅ ተግባር ላይ ‘ማህበረሰቡ እንዲህ ብናገር ምን ይለኛል?’ ያስብላል። ይህም ጭንቀት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

6. **ሁኗቀፍ አመክንዮ፡-** አመክንዮ ወይም ምክንያታዊነት አንድ ውሳኔ ለመስጠት ተጨባጭ ነገር ላይ መመስረትን የሚጠይቅ ጽንሰ ሀሳብ ነው። ይሁን እንጂ አንዳንዴ የተሟላ መረጃ ስለማይኖረን የተሟላ ድምዳሜ ላይ ላንደርስ እንችላለን፡፡

7. **የውስጥ ተቃርኖ፡-** አንዳንዴ እኛ ከምንቀበለው አስተሳሰብ ጋር የሚስማማን መረጃ ወዲያው ስንቀበል፤ ከእኛ እሳቤ ወይም እይታ ጋር የማይሄደውን፣ ትክክልም ቢሆን፣ ላለመቀበል የምናንገራግርበት ሁኔታ አለ።

**ተግባር 6**

ከላይ ከተዘረዘሩት ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አደናቃፊዎች መካከል አንተ/አንቺ ውሳኔ ስትወስን/ኚ ያጋጠሙህ/ሽ አሉ? ልምድህን ለጓደኞችህ/ሽ አጋራ/ሪ።

## ማጠቃለያ

ውሳኔ መስጠት ማለት ከብዙ አማራጮች ውስጥ በጣም ምክንያታዊ እና ተገቢ የሆነውን በመቀበል መደምደሚያ ላይ መድረስ ማለት ነው። ትክክለኛ እና ምክንያታዊ ውሳኔዎችን መስጠት ትእግስት እና ችሎታ ይጠይቃል። በተጨማሪም ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ማሰብ፣ ማመዛዘን እና ምክንያታዊነት የተሰኙ መሰረታዊ ባህሪያትን ይይዛል። ውሳኔ በየትኛውም የእድሜ ክልል መማር ያለብን ጠቃሚ ችሎታ ነው። ትክክለኛ ውሳኔ በመስጠት ሂደት ውስጥ ሊያጋጥሙን የሚችሉ እንቅፋቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል ለራስ ያለ አመለካከት፣ የቤተሰብ ፍላጎት፣ የጓደኞች ተጽእኖ እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከታች የቀረቡትን ሁኔታዎች በጥንቃቄ አንብብ/ቢ እና ትክክለኛውን ውሳኔ ለማድረግ ከቡድንህ/ሽ ጋር ስራ/ሪ። በተማርከው/ሽው ውሳኔ የመስጠት ደረጃ መሰረት መልስህን/ሽን ግለጽ/ጪ።

1. ከጓደኞችህ ጋር እግር ኳስ እየተጫወትክ/ሽ ነው። በድንገት አንደኛው ተጨዋች ሜዳ ላይ ወደቀ። ራሱን የሳተ ይመስላል፤ ግን አሁንም እየተነፈሰ ነው። በዚህ ክስተት ውስጥ ምን ውሳኔ ትሰጣለህ/ጪያለሽ?

የሚወሰድ እርምጃ:________________________________________

ውሳኔህ/ሽ ትክክል ነበር? ለምን? ______________________________

2. መምህር የቤትስራ ሰጥተውሃል/ሻል ነገርግን ጓደኛህ/ሽ የቤት ስራውን ስላልሰራ/ች ካንተ መቅዳት ይፈልጋል። ምን ማድረግ ይጠበቅብሃል/ሻል?

እርምጃ:______________________________________________

ውሳኔህ/ሽ ልክ ነበር? ለምን?________________________________

3. ቴሌቪዢን እየተመለከት/ሽ በመሀል መጸዳጃ ቤት ገባህ/ሽ፤ እና ስትመለስ/ሺ ታናሽ ወንድምህ/ሽ ለማየት በጣም የምትፈልገውን/ጊውን

ጣቢያ (ቻናል) ቀይሮታል። ምን ታደርጋለህ/ጊያለሽ?

እርምጃ፡ ___

ውሳኔህ ትክክል ነበር? ለምን? ___

4. አንተ/ቺ ለፈተና ማጥናት ትፈልጋለህ/ጊያለሽ። በሌላ በኩል ጓደኛክ/ሽ ካንተ ጋር እግርኳስ መጫወት ይፈልጋል። ምን ውሳኔ ትሰጣለህ/ጪያለሽ?

   እርምጃ፡ ___

   ውሳኔህ/ሽ ትክክል ነበር? ለምን? ___

5. ወደትምህርት ቤት ስትሄድ/ጂ የወደቀ ቦርሳ አገኘህ/ሽ። ጓደኛህ/ሽ ዝም ብለህ ውሰድ ቢል ምን ውሳኔ ትሰጣለህ/ጪያለሽ?

   እርምጃ፡ ___

   ውሳኔህ/ሽ ትክክል ነበር? ለምን? ___

# ምዕራፍ 4

# የአካባቢ እንክብካቤ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የአካባቢ ጥበቃ ምንነት፣ የአካባቢ ጥበቃ ፋይዳዎች፣ አካባቢን የመጠበቅ መንገዶች እና አካባቢን ባለመንከባከብ የሚከሰቱ ጉዳቶችን እንመለከታለን።

**ቁልፍ ቃላት፡-** አካባቢ፣ እንክብክቤ፣ ጉዳት፣ ብክለት እና ቆሻሻ

### ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- የአካባቢ ጥበቃን ምንነት መግለጽ፤
- የአካባቢ ጥበቃን ጥቅሞች ማድነቅ፤
- አካባቢን የመንከባከብ መንገዶችን መግለጽ፤
- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለውን ጉዳት መዘርዘር።

## 4.1 የአካባቢን ምንነት መረዳት

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

- የአካባቢን ምንነት ትገልፃለህ/ጪያለሽ።

የግንዛቤ ጥያቄዎች

- አካባቢ ማለት ምን ማለት ነው?
- በአከባቢው ውስጥ የተካተቱትን ነገሮች ዘርዝር/ሪ?

'አካባቢ' የሚለው ቃል ሰፊ ብያኔ፣ ትንታኔና ገለጻ የሚቀርብበት ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች 'አከባቢ' የሚለውን ቃል የሚገልጹት የሰው እና የሰው ልጅ ያልሆኑትን (በምድር ውስጥ እና ውጪ ያሉ ነገሮች) መልከዓ ምድራዊ ባህሪያት እና ተፈጥሯዊ ሂደቶችን ለማካተት ነው። በአጠቃላይ ብያኔ አካባቢ ማለት በዙሪያችን ያሉ ነገሮች ማለት ነው። ስለዚህም አካባቢ ሁሉን አቀፍ ስርዓት ነው። አካባቢ ለመኖር የሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ አሉት። ስለዚህ አካባቢን በደንብ የምንንከባከብ ከሆነ የምንፈልገውን ማግኘታችን ይቀጥላል።

ተግባር 1

አካባቢ ማለት ምን ማለት ነው?

## 4.2. የአካባቢ ጥበቃ ምንነት

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- አካባቢያችንን እንዴት መንከባከብ እንደምትችል/ዪ ትገልፃለህ/ጪያለሽ፤
- ለአካባቢ ያለህን/ሽን ፍቅር ታሳያለህ/ሽ።

የግንዛቤ ጥያቄዎች

- አካባቢን መንከባከብ ማለት ምን ማለት ነው?
- አካባቢያችንን እንዴት መንከባከብ እንችላለን?

አካባቢን መንከባከብ አካባቢያችንን ለኑሮ ምቹ ለማድረግ የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ ያጠቃልላል። ለምሳሌ ዛፎችን መትከል፣ ቆሻሻን ባገኘነዉ ሁሉ ቦታ አለመጣል እና የዱር አራዊትን መንከባከብን መጥቀስ ይቻላል።

አካባቢያችንን ለመንከባከብ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን። የኦሮሞ ማህበረሰብ በአካባቢ እንክብካቤ ላይ ፍልስፍና እና ህጎች አሉት። በዚህም መሰረት "መጀመሪያ ከራስህ ጋር ታረቅ ከዛም ከጎረቤትህ ጋር ታረቅ ከዚያም አካባቢህን በመንከባከብ ሰላም ሁን" ይላል። በዚህ ረገድ የኦሮሞ ማህበረሰብ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ካወጣቸው የሥነ ምግባር ደንቦች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ቀጥ ያሉ ዛፎች አይቆረጡም፤
- እንስሳትን ካጠጣህ/ሽ በኋላ ማጠጫውን ለሌሎች ይሆን ዘንድ በውኃ ሙላ/ዪ፤
- ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ የዱር እንስሳትን የሰዎች ስም በመስጠት ጠብቅ/ቂ።

አካባቢያችንን አረንጓዴ ለማድረግ ብዙ መንገዶች አሉ። የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ከተንከባከብን ለመጪው ትውልድ የተሻለ አካባቢን እናወርሳለን። ስለዚህ የተፈጥሮን ስነ ምህዳር በመጠበቅ አካባቢያችንን መንከባከብ የሁላችንም ግዴታ መሆን አለበት።

ተግባር 2

1. አካባቢን መንከባከብ ምን ማለት እንደሆነ አብራራ/ሪ?
2. የኦሮሞ ማህበረሰብ የአካባቢ ጥበቃ ስነምግባር ደንቦችን ጻፍ/ፊ?

## 4.3. የአካባቢ ጥበቃ አስፈላጊነት

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- አካባቢያችንን መንከባከብ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ትገልፃለህ/ሽ፤
- የአካባቢ ጥበቃ ጥቅሞችን ትዘርዝራለህ/ሽ።

የግንዛቤ ጥያቄ

1. አካባቢን የመንከባከብ አንዳንድ ጥቅሞችን ተናገር/ሪ።

አካባቢያችን ለሰው ልጅ ህይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ይዟል። ለምሳሌ የምንበላውን፣ የምንጠጣውን፣ የምንለብሰውን፣ የምንተነፍሰውን አየር እና ሌሎች ለመኖር የሚያስፈልጉንን ነገሮች የምናገኘው ከአካባቢ ነው። በአካባቢ ላይ የምናደርጋቸው ድርጊቶች ሰዎችን እና አካባቢውን ችግር ላይ ሊጥል ይችላል። ከአካባቢ ጋር ያለን ግንኙነት ለአካባቢ ተስማሚ መሆን አለበት። አንድን ድርጊት ከማድረጋችን በፊት በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አለው ወይ ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። አካባቢን መንከባከብን ባህል ማድረግ አለብን። የአካባቢ ጥበቃ አንዳንድ ጥቅሞች፦

## ሀ. አካባቢያችንን ለኑሮ ምቹ ለማድረግ

አካባቢን መንከባከብ ራስን መጠበቅ ነው። ለምሳሌ በዙሪያችን ያለውን ውሃ ብንበክል ንጹህ ውሃ ማግኘት አንችልም። እንዲሁም ዛፎችን ከቆረጥን ዝናብ ልናጣ እና በረሃብ ልንሰቃይ እንችላለን። ስለዚህ እራሳችንን የምንወድ ከሆነ አካባቢያችንን መንከባከብ አለብን። አካባቢያችንን በሚገባ የምንንከባከብ ከሆነ የተፈጥሮ የአየር ንብረት ሚዛን የተጠበቀ ይሆናል። ለምሳሌ ዝናብ በወቅቱ ይዘንብልናል።




ምስል 4.1 እንክብካቤ የተደረገለትና መልሶ የለማ አካባቢ

### ለ. ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት እና መኖሪያቸውን ለመጠበቅ፣

እንስሳት ምግብና መጠለያ የሚያገኙት ከደን በመሆኑ እንስሳቱ ያለ ምግብና መጠለያ እንዳይሰደዱ ደኑን መጠበቅ ያስፈልጋል።

ለሰው ልጅ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን እንደ ምግብ፣ መጠለያ እና አየር ያሉ በዙሪያችን ካሉ ነገሮች እናገኛለን። ስለዚህ አካባቢን መጠበቅ የሰው ልጆች ሁሉ ባህልና ስነ ምግባር ሊሆን ይገባል።

### ሐ. የሙቀት መጨመርን ለመቆጣጠር

በጣም ውስን የምንለው የሙቀት መጨመር እንኳ በአካባቢያዊ ስሪቶች ላይ ያልተጠበቀ ለውጦች እንዲከሰቱ ሊያደርግ ይችላል፡፡ አማካይ ከሆነው በላይ የአካባቢ ሙቀት መጨመር የተለመዱት ወቅቶች ላይ ለውጥ እንዲከሰት ያደርጋል፡፡ ይህም ዕጽዋትም ሆኑ ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋል፡፡

**ተግባር 3**

1. አካባቢን መጠበቅ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ አስረዳ/ጂ።
2. አካባቢን ለምን መንከባከብ ያለብን ይመስልሃል/ሻል?

## 4.4. አካባቢን የመንከባከቢያ መንገዶች

**ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- አካባቢን ለመጠበቅ የሚረዱ መንገዶችን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ።

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

- አካባቢህን/ሽን መንከባከብ የምትችልበትን/ቺይበትን መንገዶች ተናገር/ሪ።
- የቧንቧ ውሃ ከተጠቀምክ/ሽ በኋላ ዘግቶ የመሄድ ልምድ አለህ/ሽ?

አካባቢን የምንጠብቅባቸው አንዳንድ መንገዶች፡-

### ሀ. ቆሻሻን መቆጣጠር

የአካባቢ ቆሻሻን መቆጣጠር ማለት ደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻን መለየትና ከዚያ በኋላ ማስወገድ ነው። የቆሻሻ ክምችትን ከማስወገድ በተጨማሪ ቆሻሻን መቀነስ ብክለትን ለመቀነስ በጣም ጥሩው እርምጃ ነው።

### ለ. የውሃ ጥበቃ

ሁሉንም የውሃ ምንጮች መንከባከብና መጠበቅ አለብን። በውሃ ምንጮቻችን ላይ በካይ ነገሮችን መጨመር ተገቢ አይደለም። ለመጠጥ የምንጠቀመውን የቧንቧ ውሃም ሆነ ሌሎችን ሳይባክኑ መጠቀም አለብን። ለዚህም ህጋዊ እና ሞራላዊ ግዴታዎች አሉብን።

### ሐ. ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ የኃይል ምንጮችን መጠቀም

ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ እንደ ኤሌክትሪክ፣ የፀሀይ እና የንፋስ ኃይሎችን መጠቀም። እነዚህ አማራጮች የካርበን ልቀት ስለሌለባቸው አካባቢ ላይ ጉዳት አያስከትሉም።

### መ. አካባቢን የሚበክሉ ኬሚካሎች መቀነስ

በግብርና ላይ ብዙ ኬሚካሎችን የምንጠቀም ከሆነ ኬሚካሎች ወደ አፈርና ውሃ ገብተው የመሬት አሲዳማነትን ያስከትላሉ። እነዚህ ኬሚካሎች ከውሃ ጋር ከተዋሃዱ በእፅዋት፣ በእንስሳትና በሰዎች ጤና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያመጡ ይችላሉ። ስለሆነም ለምሳሌ የተፈጥሮ ማዳበሪያን ከእንስሳትና ከእጽዋት ከሚገኙ ውጋጆች አዘጋጅቶ በመጠቀም ጉዳቱን መቀነስ ይቻላል።

## ተግባር 4

1. አካባቢን መጠበቅ የምንችልባቸውን ዘዴዎች ዘርዝር/ሪ?
2. የውሃ ጥበቃ ለምን ያስፈልጋል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ታስቢያለሽ?



ምስል 4.2 ችግኞችን በመትከል አካባቢን መንከባከብ

## 4.5. አካባቢን ባለመንከባከብ የሚከሰት ጉዳት

### ቢያንስ ልትጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለውን ጉዳት ትለያለህ/ያለሽ፤
- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለውን ጉዳት ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ።

የግንዛቤ ጥያቄ


- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለውን ጉዳት ተናገር/ሪ።
- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትላቸው አንዳንድ ጉዳች፡-

## ሀ. የውሃ እጥረት ይከሰታል

ለአካባቢያችን እንክብካቤ አለማድረግ ብክለት እና የአካባቢ መራቆት ያስከትላል። በዚህም የተነሳ የዝናብ እጥረት ይከሰታል፤ ያለን የውሃ መጠን ይቀንሳል፡፡ ይህም የሰዎች፣ የእንስሳትና የተክሎች ህልውና አደጋ ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል። በውሃ እጥረት የተነሳ ሰዎች አካባቢያቸውን ጥለው ይሰደዳሉ፣ እንስሳት ይሞታሉ፣ ዕጽዋቶችም ይመናመናሉ።

## ለ. አየር ይበከላል

ተሽከርካሪዎችና የተለያዩ ፋብሪካዎች ጎጂ የሆኑ ጋዞችን ወደ አካባቢ በመልቀቅ አካባቢን ይበክላሉ። የአየር ብክለት በሰው ጤና ላይ ጉዳት ከሚያስከትሉ ነገሮች ቀዳሚው ነው። በተጨማሪም የአየር ብክለት ለአለም ሙቀት መጨመር ምክንያት ነው። የሙቀት መጨመር ደግሞ የአየር ሁኔታን በማዛባት እንደጎርፍ፣ አውሎ ንፋስ ያሉ ተፈጥሯዊ ክስተቶችን ያስከትላል።



ምስል 4.3 የአካባቢ ብክለት

## ሐ. የምግብ እጥረት

የምግብ እጥረት ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ በሆኑ ምክንያቶች ይከሰታል፡፡ የደኖች መጨፍጨፍ፣ የአፈር ለምነት ማጣት፣ የሙቀት መጠን መጨመር፣ ጎርፍ የመሳሰሉት ተግዳሮቶች የምግብ ዋስትናን ያሳጣሉ። እነዚህን ተግዳሮቶችም አካባቢን በአግባቡ ባለመንከባከብ የሚከሰቱ ናቸው። ስለሆነም አካባቢያችን በመንከባከብ የምግብ እጥረትን መቋቋም ይኖርብናል፡፡

## መ. የብዝኀ ህይወት መጥፋት

አካባቢያችንን ባለመንከባከብ ምክንያት ሊከሰቱ ከሚችሉት ክስተቶች አንዱ የተለያዩ ዝርያዎች መጥፋት ነው። ይህ የዝርያ መጥፋት ለሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያሳጣናል። ለምሳሌ አንዳንድ የመድኃኒት ተክሎች ሊጠፉ ይችላሉ ይህም ለእኛ ትልቅ ኪሳራ ነው። እንዲሁም ቀደም ሲል የምናውቃቸው የተለያዩ ዕፅዋት እና እንስሳት ከጠፉ የአካባቢያችን ውበት ይቀንሳል።



ምስል 4.4 የእንስሳት እልቂት

### ተግባር 5

1. አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ምን ምን ነው?
2. አካባቢ ቢበከል በዋነኛነት የሚጎዱት እነማን ናቸው?

# ማጠቃለያ

በዚህ ምእራፍ የአካባቢ ጥበቃን ጽንሰ ሃሳብ፣ የአካባቢ ጥበቃን አስፈላጊነት፣ አካባቢን የመንከባከብ መንገዶች እና አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለውን ጉዳት ተምረሃል።

አካባቢን መጠበቅ ማለት አካባቢያችንን ለመኖሪያ ምቹ ለማድረግ የምንወስዳቸውን እርምጃዎች ማለትም ዛፎችን መትከል፣ ቆሻሻን አለአግባብ አለማስወገድ እና የዱር አራዊትን መንከባከብ ወዘተ ይጨምራል።

አካባቢን መንከባከብ ብዙ ጥቅሞች አሉት። እነዚህም፡- አካባቢያችንን ለኑሮ ምቹ ለማድረግ፣ ሕይወት ላላቸው ፍጥረታት ምግብና መድሃኒት ለማግኘት፣ የአካባቢ ሙቀትን ለመቀነስ ወዘተ ናቸው።

አካባቢያችንን ካልተንከባከብን ለብዙ ጉዳቶች ልንጋለጥ እንችላለን። አካባቢን አለመንከባከብ ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች መካከል አንዳንዶቹ፤ የዝናብ እጥረት፣ የአየር ብክለት፣ የምግብ እጥረት እና የብዝኃ ህይወት መጥፋት ናቸው።

# የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ትእዛዝ I፡** ከዚህ በታች ያሉት ዐረፍተነገሮች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ/ሺ።

1) ሰዎች በአካባቢ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖዎች ሊኖራቸው ይችላል።
2) ተክሎች ለአካባቢ ጎጂ የሆነ አየር በማመንጨት የሚታወቁ ናቸው።

**ትዕዛዝ II.** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ።

1) አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደምንችል የሚያሳየው የትኛው ነው?
   - ሀ. ቆሻሻን አላግባብ ማስወገድ
   - ሐ. ደንን መጨፍጨፍ
   - ለ. የውሃ ብክነት
   - መ. ሙቀትን መቆጣጠር
2) አንድ ሰው ቆሻሻ ሲጥል ካየን ምን ማድረግ አለብን?
   - ሀ. ንቆ ማለፍ
   - ለ. ማበረታታት
   - ሐ. ቆሻሻውን በተወሰነ ቦታ እንዲያስወግዱ መምከር
   - መ. ቆሻሻውን መበተን
3) በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው የትኛው ነው?
   - ሀ. ዛፎችን መትከል
   - ሐ. ስለአካባቢ ጥበቃ ግንዛቤ መፍጠር
   - ለ. የተፈጥሮ ሀብቶች ብክነት
   - መ. ምክንያታዊ የሀብቶች አጠቃቀም
4) እንክብካቤ ማለት፡-
   - ሀ. የሀብት ብክነት
   - ሐ. ሀብት ማፍራት
   - ለ. ሀብትን ማጋራት
   - መ. ንብረትን ከጉዳት መጠበቅ

**ትዕዛዝ III፡** ባጭሩ መልስ/ሺ።

1. አካባቢን መጠበቅ የሚቻልባቸውን አንዳንድ መንገዶች ዘርዝር/ሪ።
2. የአካባቢ ጥበቃ እጦት የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?

# ምዕራፍ 5

# የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን የተመለከተ ነው። በዚህም መሰረት የማህበራዊ ሚዲያን ምንነት፣ አይነት፣ አስፈላጊነት፣ ስነ-ምግባራዊ አጠቃቀም አስመልክቶ ገለጻ ያቀርባል። ከዚህ በተጓዳኝም ማህበራዊ ሚዲያን አለአግባብ መጠቀም የሚያስከትለውን ጉዳት ያስረዳል።

እንደ ኮምፒውተር ያሉ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በመጠቀም በበይነ መረብ እየታገዙ መማር ቀጣይነት ባለው መልኩ ጥራት ያለው ትምህርት ለማግኘት በጣም ጠቃሚ ነው። ይሁን እንጂ በይነመረብ ላይ የምናገኛቸውን ማህበራዊ ሚዲያዎችን መጠቀም የራሱ የሆነ የአጠቃቀም መርህ አለው። መርሆቹን ተከትለን የማንገለገልበት ከሆነ ከፍ ያለ ጉዳት በግለሰብና ማህበረሰብ ላይ ሊያመጣ ይችላል። ስለሆነም ማህበራዊ ሚዲያዎችን በተገቢው መንገድ ልንጠቀምባቸው ይገባል።

### ጽንሰ-ሀሳቦችና ቁልፍ ቃላቶች

ማህበራዊ ሚዲያ፣ የግል ምስጢርን መነጠቅ፣ ምስጢርን መዝራት፣ በአግባቡ መጠቀም፣ ድር (ድረ-ገጽ)፣ አላግባብ መጠቀም፣ የሀሰት ንግግር፣ ስድብ፣ ትንኮሳዎች፣ መሳለቂያዎች

## ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-

- ማህበራዊ ሚዲያ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳት፣
- የማህበራዊ ሚዲያ አይነቶችን መዘርዘር፣
- የማህበራዊ ሚዲያን አስፈላጊነት ማስረዳት፣
- የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባርን ማሳየት፣
- የማህበራዊ ሚዲያን አላግባብ ከመጠቀም የሚመነጩ ጉዳቶችን መለየት።

# 5.1. የማህበራዊ ሚዲያ ምንነት

## ተማሪዎች ቢያንስ ሊጐናፀፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-


ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የማህበራዊ ሚዲያን ምንነት ትገልጻለህ/ትገልጫያለሽ;
- የማህበራዊ ሚዲያ አይነቶችን ትዘረዝዝራለህ/ትዘረዝሪያለሽ።

የግንዛቤ ጥያቄዎች

- ስለማህበራዊ ሚዲያ ምን ሰምትህ/ሽ ታውቃለህ/ቂያለሽ?
- ማህበራዊ ሚዲያ ምንድን ነው?

ማህበራዊ ሚዲያ በይነ መረብን (ኢንተርኔትን) መሰረት ያደረገ መስተጋብር የመፍጠሪያ መንገድ ነው። ማህበራዊ ሚዲያ ሃሳቦችን በመጋራት ወይም ከሌሎች ጋር በመነጋገር ብቻ የተገደበ አይደለም። ማህበራዊ ሚዲያ ድንበሩን ወደ ሌሎች መስኮች እና ትምህርት እያሰፋ ያለ አዲስ ዘርፍ ነው። ማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎቶቹን በምስል፣ በድምጽ፣ በድምጽና በምስል፣ በጽሁፍ እና በመሳሰሉት መልኮች ማስተላለፍ ይችላል። ማህበራዊ ሚዲያ እየተባሉ በስፋት ከሚታወቁት መካከልም ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ዩቲዩብ፣ ኢንስታግራም፣ እና ትዊተር ይጠቀሳሉ።




ምስል 5.1 ማህበራዊ ሚዲያን በአግባቡ መጠቀም

ተግባር 1

1. ማህበራዊ ሚዲያ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ማህበራዊ ሚዲያ የሚባሉት እነማን ናቸው?

## 5.2 የማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነት

### ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የማህበራዊ ሚዲያ ጠቀሜታን ትለያለህ/ያለሽ።
- የማህበራዊ ሚዲያ ጥቅሞችን ትረዳለህ/ጂያለሽ
- የማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነትን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ
- ማህበራዊ ሚዲያ ምን ምን ጠቀሜታዎች እንዳሉት ማስረዳት ትችላለህ/ያለሽ

የግንዛቤ ጥያቄ

- ማህበራዊ ሚዲያዎች ምን ምን ጠቀሜታዎች እንዳላቸው ማስረዳት ትችላለህ/ያለሽ?

የማበረሰባችንን እሴቶች በመከተል ማህበራዊ ሚዲያን በአግባቡ ከተጠቀምንበት ከበርካታ ሰዎች ጋር በተመሳሳይ ጊዜ መስተጋብር እንድንፈጥር፣ ወቅታዊ መረጃን እንድንለዋወጥና ተግባቦትን እንድናሳልጥ ይረዳናል። እንዲሁም በየትኛውም የአለም ጥግ የተከሰተ ጉዳይ ወዲያውኑ እንዲደርሰን ያስችላል። ተማሪዎችም በአግባቡ የሚገለገሉበት ከሆነ እውቀታቸውን እንዲያሰፉና እና ልምዶቻቸውን እንዲያጎለብቱ ያግዛቸዋል። ከማህበራዊ ሚዲያ የምንወስዳቸው መረጃዎች ግን ከትክክለኛና ከታማኝ ምንጮች የተገኙ መሆን ይኖርባቸዋል።

ተግባር 2

የማህበረሰብን ወግ ባልተጻረረ መልኩ ከተጠቀምንባቸው ማህበራዊ ሚዲያዎች ምን ምን ጠቀሜታዎች ይሰጣሉ?

## 5.3. የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች:-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባርን በመረዳት ትተገብራለህ/ ሪያለሽ

የግንዛቤ ጥያቄዎች

- ማህበራዊ ሚዲያን ስንጠቀም የምንከተላቸው የአጠቃቀም ስነምግባሮች ምን ምን ናቸው?
- ማህበራዊ ሚዲያ ሲንጠቀም መከበር ያለባቸው የማህበረሰባችን እሴቶች እንዴት ያሉት ናቸው?
- ከታች ካሉት ምስል 'ሀ' እና ምስል 'ለ' ምን ትማራለህ/ሪያለሽ?

ምስል ሀ



ምስል ለ



ምስል 5.2 የሐሰተኛ መረጃ ማሳያ

የኦሮሞ ማህበረሰብ "እውነት የፈጣሪ ልጅ ነው" ብሎ እንደሚተርተው፤ እውነትን መናገር እጅግ ተገቢ ነው። ስለዚህ ሁሉም ሰው አንድን መረጃ ለሌላ ሰው ከማጋራቱ በፊት ወይም ከተቀበለ በኋላ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል። የተገኘ መረጃን ከመቀበልና እና ለሌሎች ከከማጋራት በፊት ምንነቱንና እና ይዘቱን ማወቅ የግድ ነው። ስለሆነም በማህበራዊ ሚዲያ ሀሰተኛ መረጃን ማጋራት ጎጂነቱ ከፍ ያለ ሊሆን ስለሚችል መጠንቀቅ ይገባናል። በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት የሀሰት መረጃ የሚያጋራ ሰው ሲያጋጥመንም ማስተካከያ ለመስጠት መሞከር አለብን።

በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተጨባጭ መረጃን ማካፈል ሁለት ጥቅሞች አሉት። በመጀመሪያ ሌሎችን የማሳሳት እድል አይኖረንም፤ ሁለተኛ በማንኛውም ጊዜ እምነት የሚጣልብን መሆናችንን ለህብረተሰቡ ያሳውቃልናል። ይህም ሥነ ምግባር የተላበስንና  የማህበረሰብን እሴት የምንጠብቅ ሰዎች ያደርገናል፤ በብዙ ሰዎች ዘንድም ያስከብረናል።

የእጅ ስልኮቻችንን በመጠቀም ወቅት ልንከተላቸው የሚገቡ መርሆች

1. ከማናውቀው ወይም እንግዳ ከሆነ ሰው ስልክ ቢደወልልን አክብሮትን

የሚያመላክቱ ቃላትን እንጠቀም፤
2. በስልክ የተነገረንን ነገር ሳናጣራ ለሌሎች አናጋራ፤
3. የማህበረሰብን እሴቶች የሚጻረሩ መረጃዎችን ከመስጠትም ሆነ ከመቀበል መታቀብ አለብን፤
4. የግለሰቡን ፈቃድ እስካላገኘን ድረስ ፎቶ ግራፍም ሆነ ቪዲዮ ቀርጸን ለሌሎች አናጋራ፤
5. ማህበራዊ ሚዲያን ለአዎንታዊ ነገሮች ብቻ እንጠቀም፤
6. ማህበራዊ ሚዲያን ለተራዘመ ጊዜ ከመጠቀም እንቆጠብ፤
7. የሰማነውን መረጃ በችኮላ በበይነ መረብ ላይ መልቀቅም ሆነ ማጋራት የለብንም፤
8. በእጃችን ያለን መረጃ ለሰዎች ከማጋራታችን በፊት ጥቅምና ጉዳቱን ማመዛዘን አለብን።

**አንድን መረጃ ለሌሎች ለማጋራት ስናስብ ልንከተላቸው የሚገቡን ነጥቦች፤**

**መረጃው፡-**

- ✓ ትክክለኛ ነው? (ትክክለኛ የሆነን መረጃ ብቻ አጋራ/ሪ)
- ✓ ለምናጋራቸው ሰዎች ጠቀሜታ አለው? (ማህበረሰብን የሚጠቅም መረጃ ብቻ አጋራ/ሪ)
- ✓ ሰዎችን ያነቃቃል? (ሰዎችን የሚያነቃቃ/የሚያበረታታ ከሆነ ብቻ አጋራ/ሪ)
- ✓ በጣም ወሳኝ ነው? (ወሳኝና ወቅታዊ የሆነ መረጃን ብቻ አጋራ/ሪ)
- ✓ መልዕክቱ ግልጽ ነው? (አሻሚ ትርጉም የያዘ መረጃ አታጋራ/ሪ)

## ተግባራት 3

1. ማህበራዊ ሚዲያን ስንጠቀም ልንከተላቸው የሚገቡንን መርሆች ዘርዝር/ሪ?
2. ማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም ወቅት ሊከበሩ የሚገባቸው የኦሮሞ ማህበረሰብ እሴቶች ምን ምን ናቸው?

## 5.4. የማህበራዊ ሚዲያ አላግባብ የመጠቀም ጉዳቶች

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ማህበራዊ ሚዲያን በአግባቡ ባለመጠቀም የተነሳ የሚከሰቱ ጉዳቶችን ትዘረዝራለህ/ትዘረዝሪያለሽ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

- ማህበራዊ ሚዲያን በተገቢው ሁኔታ ካለመጠቀም የተነሳ ሊከተሉ የሚችሉ ጉዳቶችን ታውቃለህ/ቂያለሽ?

ማህበራዊ ሚዲያን በተገቢው ሁዘኔታ አለመጠቀም የሚያስከትላቸው ጉዳቶች አሉ። ሊከሰቱ ከሚችሉ ጉዳቶች መካከል የተወሰኑት፡-

### 1. በማህበራዊ ሚዲያ የመጠቀም ሱስ መጠመድ

በማህበራዊ ሚዲያ ሱስ የተጠመዱ ተማሪዎች ብዙውን ጊዜያቸውን ያለአግባብ ያባክናሉ። ጊዜያቸውን በቤት ውስጥ እንዲያሳልፉ ስለሚያደርጋቸው ከጓደኞቻቸው ጋር ተገናኝተው የመጨዋወት እድላቸውን ያሳጣቸዋል። በዚህም የተነሳ ከጓደኛና ቤተሰብ ተነጥለው ብቸኝነት ውስጥ እንዲዘፈቁ ያደርጋቸዋል። አረጋዊያንን መንከባከብ፣ አዛውንቶችን ማክበርና እናትና አባትን መታዘዝ የመሳሰሉ ማህበራዊ እሴቶችን ይዘነጋሉ። የገቡበት ሱስ ስሜቶቻቸውን ስለሚቆጣጠረው ስነምግባርን ያስረሳቸዋል፤ መርሆችን እንዲጥሱም ያደርጋቸዋል።

### 2. መሰደብ

በማህበራዊ ሚዲያ እውነት ያልሆኑ እና ግብረገብነትን ያልጠበቁ መረጃዎችን መለጠፍ ስድብንና ዛቻን ያስከትላል። ይህም ከማህበራዊ ሚዲያ ገፆቻችን መሳደድንና አስጸያፊ ቃላት መሰንዘርን ያመጣል።

## 3. የስሜት መጎዳት

የተፈጠረው አንድ ስህተት ሁልጊዜ ስህተት እንደምንሰራ በማስቀጠር በማህበራዊ ሚዲያው በኩል ተቀባይነትን ያሳጣል። በዚህም የስሜት መጎዳት ይከሰታል፡፡ ይህ ክስተት አንዳንዴ ግላዊ ምስጢርን ከማሰራጨት ሊመነጭ ይችላል።

## 4. መወገዝ

በማህራዊ ሚዲያ አማካኝነት የሀሰት መረጃ መንዛት ማህበራዊ እሴቶችን መጣስ ነው። በማህበራዊ መርህ የሚዋሽ ሰው ይጠላል፣ ይወገዛል። ስለሆነም የሀሰትና እውነትነቱ ያልተረጋገጠ መረጃ ማጋራት አያስፈልግም።

## 5. ለትንኮሳ ያጋልጣል

ጾታዊና መሰል ትንኮሳዎች እንዲከተሉ በር ይከፍታል።

### ተግባር 4

1. ማህበራዊ ሚዲያዎችን ከመጠን በላይ መጠቀም ምን አደጋዎች አሉት?
2. ማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም ወቅት የተከለከሉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

## የጉዳይ ጥናት

አጎቴ እና ሞሚና ጓደኛሞች ናቸው። ከ5ኛ ክፍል ጀምረው አብረው ይማሩ ነበር። አጎቴ ከትምህርት ቤት እንደተመለሰ የእናቱን ስልክ በመያዝ የተለያዩ ጌሞችን መጫወት ያዘወትራል። ጌሞቹን መጫወት ሲሰለቸውም ወደ ማህበራዊ ሚዲያዎች ጎራ እያለ የተለያዩ ልጥፎችን ያያል። ይህ የየዕለት ተግባሩም ሱስ እየሆነበት መጣ። ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድም ከነዚህ ሚዲያዎች ያገኘውን መረጃም ሳያጣራ ለጓደኞቹ ይነግራቸው ነበር። ይሁን እንጂ ጓደኞቹ የሀሰት ወሬ እንደሚያሰራጭ ስለደረሱበት መሳለቂያ በማድረግ የተገለለ እንዲሆን አደረጉት። ይህም ብቸኝነት እንዲሰማው አደረገዉ። በተጨማሪም ብዙውን ጊዜ የቤት ሥራውን ሳይሠራ ወደ ትምህርት ቤት ስለሚሄድ፣ ከክፍል ይባረራል። በመጨረሻም ትምህርቱን ለማቋረጥ ተገደደ።

ሞሚና ግን ከትምህርት ቤት እንደተመለሰች የሚቀርብላትን ምግብ

ትመገባለች። ከምግብ በኋላም የቤት ስራዋን ትሰራለች። የቤት ስራዋን ሰርታ ከጨረሰች በኋላም ከሰፈር ጓደኞቿ ጋር ለአጭር ጊዜ ትጫወታለች። የአቅሟን ያክልም ወላጆቿን በስራ ታግዛለች። ለትምህርቷ ልዩ ትኩረትን ስለምትሰጥም ከክፍል ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ከማድረግ ባሻገር ወደ ቤተመጽሐፍም በመሄድ ታጠናለች። በዚህም ከክፍሏ ብቻ ሳይሆን እንደትምህርት ቤትም አንደኛ በመውጣት ሽልማቶችን ጠራርጋ ወስዳለች። ወደፊትም ጠንካራ የህግ ባለሙያ በመሆን ህብረተሰቧን ለማገልገል አልማለች።

**ተግባር 5**

1. የአጎቴ ጓደኞች አጎቴን መሳለቂያ እንዲሆን ያደረጉት ለምንድን ነው?
2. ሞሚና በትምህርቷ እጅግ ውጤታማ የሆነችው እንዴት ነው?

ማህበራዊ ሚዲያን በመገልገል ወቅት ክልክል የሆኑ ተግባራት

- ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር እና የይለፍ ቃልን ለሌሎች መስጠት
- ለማናውቃቸው ሰዎች ፎቶዎቻችንን ማጋራት
- የማናውቃቸውን ሰዎች ኢ.ሜይሎች እና ሰነዶችን መክፈት
- ከማናውቀው ሰው ጋር በበይነ መረብ ሀሳብ መለዋወጥ
- የነውር ቃላትን መጠቀም

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ማህበራዊ ሚዲያ እንደ ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ኢንስታግራም፣ ቴሌግራም፣ ዩቲዩብ ፣ ቲክ ቶክ የመሳሰሉ መገናኛዎን በመጠቀም መረጃ ለመቀበልና ለመስጠት አስፈላጊ ነው። እንዲሁም እውቀት ለመቅሰም እና የንግድ ስራን ለማቀላጠፍ ያስችላል።

በማህበራዊ ሚዲያ መጠቀም የራሱ የሆነ ሥነምግባር አለው። የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ዋና ዋና መርሆች የውሸት ዜናን አለማሰራጨት፣ እውነትን መለየትና መደገፍ፣ ማህበራዊ አስተምህሮቶችን የሚጥሱ የነውር ቃላትን አለመጠቀም፣ ጊዜን በማህበራዊ ሚዲያ ላይ አለማባከንና የመሳሰሉት ናቸው።

ማህበራዊ ሚድያዎችን በአግባቡ ልንገለገልባቸው ካልቻልን ከፍ ያለ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ። ከጉዳቶቹ መካከልም ዋና ዋናዎቹ በማህበራዊ ሚዲያ ሱስ መጠመድ፣ የሀሰት ወሬ በማሰራጨት የተነሳ መሰደብ፣ መሳቂያ መሳለቂያ መሆንና ከማህበረሰቡ መገለል በዚህም የተነሳ የሞራል ውድቀት መከተል ናቸው።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ትዕዛዝ I፡-** የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ 'እውነት' ትክክል ካልሆኑ ደግሞ 'ሐሰት' በል/ዪ።

1. በማህበራዊ ሚዲያ መገልገል ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም።
2. በማህበራዊ ሚዲያ ስንጠቀም የማህበረሰብን ስነምግባር የመጠበቅ ግዴታ አለብን።
3. በማህበራዊ ሚዲያ የሚሰራጩ መረጃዎች ሁሉ ትክክለኛ ናቸው።
4. ከማህበራዊ ሚዲያ የሚጠቅመንን እውቀትን ማግኘት እንችላለን።
5. የሀሰት ዜና ግለሰብን እንጂ ህብረተሰቡንና ሀገርን ሊጎዳ አይችልም።

**ትዕዛዝ II፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልስ/ሺ።

1. ማህበራዊ ሚዲያ የሚባሉትን ዘርዝር/ሪ።
2. ማህበራዊ ሚዲያን በተገቢው መንገድ ከተገለገልን ምን ምን ጠቀሜታዎችን ልናገኝ እንችላለን?

# ምዕራፍ 6

# የባህል ትስስር

## መግቢያ

በዚህ መጽሐፍ አምስተኛው ምዕራፍ የማህበራዊ ሚዲያ የስነምግባር ደንብ፣ የማህበራዊ ሚዲያ አይነቶች እና ጠቀሜታዎች ተመልክተናል። በዚህ ስድስተኛ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ባህል ምንነት፣ ጠቀሜታና በልዩ ልዩ ባህሎች መካከል ስላለው ግንኙነትና ማሳያዎቹ እንማራለን።

**ቁልፍ ቃላት፡-** ሚዲያ፣ ግንኙነት፣ መድልዎ፣ ንቃተ ህሊና፣ አቃፊነት፣ መንደር፣ ፍቅር እና ሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን)፣ ተግዳሮት

### ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ዉጤቶች፡-

- የባህል ትስስርን ምንነት መግለጽ፤
- የባህል ትስስርን አስፈላጊነት ማድነቅ፤
- ባህላዊ ትስስርን የሚያጠናክሩ አወቃቀሮችን መለየት።

## 6.1. የባህል ግንኙነቶች ምንነት

### ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- የባህል ትስስርን ምንነት ትገልፃለህ/ትገልጫለሽ፡፤
- ባህላዊ ትስስሮችን የሚያጠናክሩ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ትለያለህ/ሽ።

የግንዛቤ ጥያቄዎች

- በትምህርት ቤትህ/ሽ ውስጥ ባሉ ተማሪዎች መካከል ያለውን የባህል ልዩነት መለየት ትችላለህ/ያለሽ?
- በባህሎች መካከል ያለው ትስስር ምን እንደሆነ ታውቃለህ/ታውቂያለሽ?

ትስስር ማለት የተለያየ ቋንቋና ባህል ያላቸው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አብሮ መኖር ማለት ነው። የብሔር ብሔረሰቦች አንድ ላይ መኖር የባህል እና ቋንቋ ግንኙነትን ይፈጥራል። የባህል ግንኙነት ማለት ተጎራብተው የሚኖሩ ብሔረሰቦች በጋራ ያላቸው የባህል ትስስር ማለት ነው። ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የየራሳቸው ባህል፣ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ወግ፣ ፍልስፍና የመሳሰሉትን አላቸው። ለረጅም ጊዜ አብረው የኖሩ ህዝቦች ደግሞ እርስበርስ የሚሰጣጡትና የሚቀባበሉት ነገር ይኖራቸዋል። ይህ አካሄድም የባህል ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል። በዚህ መንገድ በህዝቦች መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት አንዱ ሌላውን እንዲያውቀው ስለሚያስችል በሰላምና መረጋጋት አብረው እንዲኖሩ አቅም ይፈጥርላቸዋል።

ይህም በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እርስ በርስ እርስበርስ እንዲረጋዱ ያስችላቸዋል። በሌላ በኩል አንዱ የሚወደውን እና የሚጠላውን ሌላው ስለሚረዳ ተቻችለው እንዲኖሩ ይጠቅማቸዋል። በተለያዩ ምክንያቶች ሰላማቸውን ሊያውኩ የሚችሉ ምልክቶች መታየት ከጀመሩም አስቀድመው በመነጋገር ሊያስወግዷቸው ይችላሉ። የኦሮሞ ማህበረሰብ የጋራ ጉዳት የሚያስከትሉ እንዲህ አይነት ክስተቶች ሲፈጠሩ የማስወገጃ ብልሃቶች አሉት።

የባህል ግንኙነት ማለት አንዳንድ ጊዜ በባህሎች መካከል ያለ ጥናት/ምርምር/ በመባል የሚታወቅ ሲሆን የማህበራዊ ሳይንስ አዲስ የጥናት ዘርፍ ነው። ሰዎች እንድን አላማ በተጨባጭ ተገንዝበው እንዲተገብሩት የሚያስተምር የትምህርት መስክ ነው። ከዚህም ሌላ በመሰረታዊ ደረጃ እራስንና ነባራዊውን አለም በሌሎች ሰዎች አይን ማየት እንደሚቻልም ያስገነዝባል። ይህም የተለያዩ ባህሎች ባላቸው ቡድኖች መካከል መስተጋብር እንዲፈጠር ያስችላል።

በማህበራዊ ሚዲያ፣ ድረ-ገጾች እና ቴክኖሎጂ ተፅእኖዎች የተነሳ በአሁኑ ወቅት በአለማችን 'ብሔራዊ ድንበሮች የሉም' ሊያሰኝ የሚችልበት ደረጃ እየደረሰ ነው። ይህ ሁኔታም ሰዎች ባህላቸውን እርስ በርስ እንዲናበቡና እንዲከባበሩ በማድረግ ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ ያስችላቸዋል።



ምስል 6.1. የባህል ትስስር

## ተግባር 1

1. ባህላዊ ግንኙነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ከላይ በስእል 6.1 የቀረቡትን ምስሎች ተመልከት/ቺና ያየሃቸውን/ሻቸውን ሦስት ልዩነቶች ጻፍ/ፊ።

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

## 6.2. የባህል ትስስር አስፈላጊነት

### ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- በባህሎች መካከል በሚኖር ግንኙነት የሚገኙ ጥቅሞችን ትዘረዝራለህ/ሽ
- በባህል ትስስር የተነሳ እርስ በርስ መማማር እንደሚቻል ታደንቃለህ/ሽ።

በአለማችን ላይ የተለያዩ ባህሎች የሚገኙ ሲሆን፣ እነዚህም በአሁኑ ወቅት ጠንካራ ግንኙነት በመመስረት ይታወቃሉ። በባህሎች መካከል ያለው ግንኙነት እየተጠናከረ ከሄደ በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። የባህል ግንኙነት ጥቅሞች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ. አዲስ ባህል መማር፤

ለ. አዳዲስ ክህሎቶችን መማር፤

ሐ. የተሳሳቱ አመለካከቶችን ማስቀረትና የመሳሰሉት

### ሀ. አዲስ ባህል መማር

አንድ ሰው ከሌሎች ባህሎች ጋር በተገናኘ ቁጥር በባህሉ ውስጥ ያገኛቸውን አዳዲስ ነገሮች እየተማረ ይሄዳል። ባህል ከድምጽ አወጣጣችን ጀምሮ እስከ የአካላዊ እንቅስቃሴ ድረስ ተግባቦት በመፍጠር ሂደታችን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው። አመለካከታችን፣ የአነጋገር ሁኔታችን፣ ከቤተሰብ አባላት ጋር ያለን ግንኙነት እና የምናልፍባቸው የአኗኗር ስርዓቶች ሁሉ ከባህል ተጽእኖ የፀዱ አይደሉም። ስለሆነም ለምሳሌ አንድ ተማሪ እሱ ጋር የሌለን ባህላዊ ጉዳይ ከሌላ ተማሪ ባህል መማር ይችላል።

### ለ. አዳዲስ ክህሎቶችን መማር

ባህል የአንድ የተወሰነ የሰዎች ቡድንን ሰፊ ልምዶች ይገልፃል። ለምሳሌ አመጋገብን፣ ጭፈራን፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴን እና አንድን ነገር የመረዳት ልምድን ያካትታል። ከባህላችን ጋር ተዛማጅነት ያላቸው አንዳንድ ክህሎቶች

አስቀድመው ሊኖሩን ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ በባህሎች መካከል በሚፈጠር ግንኙነት ደግሞ ሌሎች ተጨማሪ ክህሎቶችን ለመማር እድል ይፈጠርልናል። ለምሳሌ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚካሄዱ ባህላዊ የስፖርት እንቅስቃሴዎችን የመጋራት ወይም ጓደኞችን ከቤተሰብ አባላቱ ጋር ሲጫወት ያደገበትን ጨዋታ መማር እንችላለን። በተጨማሪም፣ ከቤተሰባችን ወይም ጓደኞችን ጋር ለመግባባት ስንል አዲስ ቋንቋ ወይም ዘዬ መማር እንችላለን።

## ሐ. የተሳሳቱ አመለካከቶችን ማስወገድ

ሰዎች ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችና ሰዎች በባህል ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ የያዙት ያልተገባ እይታ ወደ ትክክለኛ መስመሩ መመለስ አለበት። የባህል ትስስር ደግሞ እንዲህ ያለውን ጉዳት ያስወግዳል ወይም ያሳንሰዋል። ባህላዊ ግንኙነቶች መልከ ብዙ ሲሆኑ፤ በአሁኑ ወቅት በአለማችን ላይ በዘር፣ በእድሜ፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ፣ በብሄር፣ በፆታ እና በችሎታ አማካይነት መሰባሰቡ የተለመደ ሆኗል። በባህል ከማይመስሉን ሰዎች ጋር በጋብቻ፣ በጓደኝነት እና በትምህርት ቤት አማካኝነት ግንኙነት መፍጠር እንችላለን። ከእነዚህ ሰዎች ጋር በሰላም ለመኖር፣ ስለነሱ አዎንታዊ አመለካከት መያዝ ወሳኝ ነገር ነው።

በባህሎች መካከል የሚኖር ግንኙነትን ማስቀጠል ሶስት መሰረታዊ የሆኑ ማህበራዊ መሻቶችን ያሟላል። እነሱም፡-

1. በማህበረሰብ ውስጥ መታቀፍ ፡- እነዚህ 'ህዝቦቼ ናቸው' የሚል ውስጣዊ ስሜት ይፈጥራል።
2. መዋደድ፡- አንድ ሰው ለእኛ ያለውን እኛም ለሌላው ያለንን ፍቅር ያሳያል።
3. መቆጣጠር፡- በሌሎች ላይም ሆነ በራስ ላይ ለውጥ የማምጣት አቅም ነው።

ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ሰዎች በሌሎች የመታቀፍ፣ የመወደድ እና የመቆጣጠር ፍላጎቶችን በተለያዩ መንገዶች ያሳካሉ። ለምሳሌ በአንዳንድ ባሕሎች አንዲት ሴት ለወንድነቱ አክብሮት እንድትሰጥለት ለማትጋት በር

መከፈት ይጠበቅበታል። በሌላ ባህል ደግሞ ወንድ ለሴቷ ክብር ለመስጠት ሲል እሷን አስቀድሞ በጥቂት ርቀት እየተከተለ መሄድ ይጠበቅበታል። ይህ የሚያሳየው ግንኙነቶቹ ከባህል ወደ ባህል የሚለያዩ መሆናቸውን ነው።

ተግባር 2

1. የባህል መስተጋብር አስፈላጊነት ወይም ጠቀሜታ ምንድን ነው?

## 6.3. ባህል እና ሉላዊነት

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጐናፀፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች፡-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

ስለ ሉላዊነት ወይም ግሎባላይዜሽን ምንነት ታስረዳለህ/ታስረጂያለሽ፣

- ሉላዊነት በባህል ላይ የሚያስከትላቸውን ተጽዕኖዎች ታደንቃለህ/ታደንቂያለሽ።

**የግንዛቤ ጥያቄ**

- ስለሉላዊነት ምን ታውቃለህ/ታውቂያለሽ?

ባለንበት ወቅት ሉላዊነት የዓለማችንን ህዝቦች አንድ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። ይሁን እንጂ መለያየት (መድልዎ) እና አለመቻቻል በዚህ ዓለም ላይ ጉዳት እያስከተሉ ነው። ይህ ሁኔታ ብዝሃ ባሕላዊነት እየጨመረ ባለበት ወቅት በብሔረሰቦች መካከል የእኩልነት እሳቤ እንዲመናመን ሊያደርግ ይችላል።

በሁለት የተለያዩ ባህሎች መካከል የሚኖር መስተጋብርን መፍጠር ፈታኝ ጉዳይ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ሲካሄዱ የነበሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ ሰዎችን በባህላዊ ቡድኖች መከፋፈል ወደ ተሳሳተ አመለካከት ሊመራ እንደሚችል ይጠቁማሉ። ይህም በአንድ ባህል ውስጥ ያለ ቡድን የሌላ ቡድን ባህል የተሳሳተ

ነው ብሎ እንዲያስብ ሊያደርገው ይችላል። ከራሳቸው ባህል ጋር የሚመሳሰሉ ባህሪያት ያላቸውን ቡድኖች እንደ ጥሩ እና ከባህሪያቸው ጋር የማይመስሉ ቡድኖችን ባህል ደግሞ እንደ መጥፎ ቆጥረው ሊመለከቷቸው ይችላሉ። ከእኛ ጋር ለሚመሳሰሉት መልካም ስም የመስጠትና የማይመሳሰሉትን ደግሞ የማጠልሸት አካሄድ መድልዎን ያስከትላል። በዚህ መልኩ የተለያዩ ባህሎች ባላቸው ቡድኖች መካከል የሚፈጠር መድልዎ ወደ ግጭት ሊያመራ ይችላል።

አድልዎ እና የተዛባ አመለካከት በፆታ፣ በማህበራዊ መደብ፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ ወይም በስብዕና ባህሪያት ላይ ተከስቶ ሊታይ ይችላል። ይህም በስራ እድል ማግኘት፣ በትምህርት፣ በመኖሪያ ቤት፣ በፖለቲካዊ መብቶች እና በመሳሰሉት ሊንጸባረቅ ይችላል። ይህ ደግሞ በባህላዊ ግንኙነቶች ላይ እንቅፋት ይፈጥራል። ስለዚህ የራሳችንን ባህል የምንወደውን ያህል ሌሎች ሰዎችም ባህላቸውን እንደሚወዱ በማወቅ በባህሎች መካከል ያለውን ትስስር ለማጠናከር መጣር አስፈላጊ ነው። በባህሎች መካከል ያለውን አዎንታዊ ግንኙነት ማጠናከር ዛሬ ባለው ዓለም ውስጥ ወሳኝ የህይወት ክህሎት ነው።

የሉላዊነት እድገት በባህሎች እና ማህበረሰቦች መካከል መተሳሰር እና መደጋገፍ እየፈጠረ ነው። ይህ ማለት ግን ግንኙነቱ አንድ አይነት ባህል ብቻ ያላትን አለም ይፈጥራል ማለት እንዳልሆነም መረዳት ይኖርብናል። እንዲሁም አለም በቴክኖሎጂ ተሳሰረች ማለት አንድ ድንበር አሰመረች ማለት እንዳልሆነም ልብ ማለት ያስፈልጋል።

በሉላዊነት ሂደት ውስጥ ግለሰቦች እና ማህበረሰቦች በመልክዓምድራዊ ርቀት ያልተገደቡ እንደሆኑና እና ማህበራዊ የግንኙነት ስርዓታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ከማሳየቱም በላይ እውቅናውም እያደገ ለመምጣቱ ማሳያ ነው።

የእርስ በርስ ግንኙነት እየጨመረ መጣ ማለት ዓለም አቀፋዊ የባህል ልዩነቶች እንዲወገዱ ተደርገው ወደ አንድ ባህል እየተጠቃለሉ መጡ ማለት አይደለም። አዳዲስ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች ሰዎችን የሚያቀራርቡ ናቸው ማለትም አንድ መልክ ብቻ ባላት ዓለም ውስጥ እንሳተፋለን ማለት እንዳልሆነም ልብ ማለት

ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ የምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ እርስበርስ ጥገኝነቱ እና የመጓጓዣ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች መስፋፋት 'የእኔ ባህል ብቻ ነው ትክክል' የሚለውን አስተሳሰብ እንዲሸረሸር እያደረገው ይገኛል።

በሌላ በኩል ለባህል ዕድገት መልካም አጋጣሚዎች እየተፈጠሩ መሆኑን ያመላክታል። ለምሳሌ አዳዲስ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች መስፋፋት በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች በቀጥታ በመገናኘት ተግባቦት እንዲያሳልጡ አስችሏቸዋል። በአንደኛው የአለም ጥግ ያሉ ተመልካቾች በሌላኛው የአለም ክፍል የተፈጠሩ አሁናዊ ክስተቶችን በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ። በተመሳሳይ ጊዜ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች አገር በቀል ባህሎች የራሳቸውን ሚዲያ እንዲፈጥሩ እና በሌሎች አገሮች የሚኖሩ ዜጎች ባሉበት ሆነው ከአካባቢያቸው ማህበረሰቦች ጋር ግንኙነታቸውን እንዲያስቀጥሉ ያስችላቸዋል። ይህ ሁኔታ ዓለምን ወደ አንድ ቋት አምጥቷታል።

በሁለት የተለያዩ ባህሎች መካከል ትስስር ለመፍጠር በሚሞከርበት ወቅት ትልቁ እንቅፋት የሚሆነው የሌላውን ባህል የበታች አድርጎ የመመልከቱና 'የእኔ ባህል ብቻ ልክ ነው!' ብሎ የማሰቡ ጉዳይ ነው። ይህ የራስን ባህል ወይም ማህበረሰብ ብቻ ማዕከል አድርጎ የመሄዱ ነገር ለሌሎች ማህበረሰቦች ባህል ከተያዘ የተሳሳተ አመለካከት የሚመነጭ ነው። የተሳሳተ አመለካከት መያዝ ደግሞ በሌሎች ብሔሮች ባህል ውስጥ ያለውን እውነታ እንዳንረዳ ያሰናክለናል። ስለሆነም ተከባብረው በጋራ ለመኖር ሰዎች ከተሳሳቱ አመለካከቶችና መድልዎ እራሳቸውን ማራቅ አለባቸው።

ባህላዊ መስተጋብር የራሱ የሆነ መርህ አለው። ይህ መርህም ከባህል ባህል ልዩነት ይኖረዋል። ተግባቦትን ስናከናውን በሌላው ባህል ውስጥ ስላለው ሥርዓት ላንረዳ እንችላለን። በዚህም የተነሳ ለሌላው ለባህል የምንይዘው የተሳሳተ አመለካከት ወይም የግንዛቤ ማነስ ሁኔታውን የበለጠ ያባብሰዋል ወይም ከዚያ ባህል ጋር ስምሙ እንዳንሆን ያደርገናል።

ተግባር 3

1. የኔ ባህል ብቻ ነው የተሻለው ብሎ ማለት በባህሎች መካከል ባለ መስተጋብር ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ያመጣል?
2. የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ተመሳሳይ የሆነ ባህል ሊኖራቸው ይችላል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ታስቢያለሽ?
3. ተመሳሳይ ባህልን እያጎለበቱ መሄድ ምን ችግር ያመጣል?

## 6.4. የባህል ትስስር መገለጫዎች

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፏቸው የሚገቡ የመማር ብቃቶች:-**

ከዚህ ትምህርት በኋላ:-

- በባህል መስተጋብር ውስጥ የሚያስፈልጉትን የግንኙነት ዓይነቶች ትለያለሽ/ትለያለህ፤
- በባህል መስተጋብር ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉ ነገሮችን ትገልጻለህ/ትገልጫለሽ።

### 6.4.1 ውጤታማ መስተጋብር

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

- ውጤታማ የሆነው መስተጋብር ምንድን ነው?
- ከጓደኞችህ/ሽ ጋር ያለህ/ሽ ግንኙነት ውጤታማ ነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያለሽ?

ውጤታማ መስተጋብር ማለት አስተሳሰብን፣ እውቀትን እና መረጃን በመለዋወጥ አንድ የታለመ ግብ ወይም አላማ በጥሩ ሁኔታ እንዲሳካ የማድረግ ሂደት ነው። በቀላል አነጋገር፣ መልዕክት ተቀባዩ የመልዕክት አቀባዩን ሀሳብ በአግባቡ መረዳት መቻሉ ነው። ውጤታማ መስተጋር የሚከተሉትን ያጠቃልላል:-

ሀ. **መልዕክት አቀባይ** - መልእክት በመላክ የግንኙነት ሂደቱን የጀመረው ሰው አቀባይ ይባላል።

ለ. **ተቀባይ** - መልእክቱ የተላከለት ሰው ተቀባይ ይባላል።

ሐ. **መልእክት** - ከላኪ ወደ ተቀባዩ የሚሄድ ጭብጥ ወይም ሀሳብ።

ተግባር 4

ተማሪዎች! መምህራችሁ ለክፍል ጓደኛችሁ በየተራ እንድታስተላልፉ በሚስጢር የሚነግሯችሁን መልዕክት መመሪያውን ተከትላችሁ በሹክሹክታ አድርሱ። በመጨረሻም መምህር ለመጀመሪያው ተማሪ የነገሩትንና የመጨረሻው ተማሪ የሰማው መልዕክት ተመሳሳይ መሆኑን አነጻጽሩ።

1. በመጀመሪያው መልእክት እና በመጨረሻው መካከል ልዩነት አለ?
2. ካለ ልዩነቱ የተከሰተው በምን ምክንያት ነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ ታስቢያለሽ?

ውጤታማ የሆኑ መስተጋብሮች ባህሪያት

በተግባቦት ወቅት መልዕክት ማስተላለፍ ብቻውን በቂ አይደለም። የመልዕክት ላኪው አላማ ግቡን መምታት አለበት። ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት መረጃን ውጤታማ የሚያደርጉት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ግልጽ የሆነ መልዕክት፡- መልዕክት አቀባዩ የሚያስተላልፈው መልእክት በቀላሉ ለመረዳት የሚቻል እና በሥርዓት የተቀመረ መሆን አለበት።
- ትክክለኛ መልእክት፡- የሚተላለፈው መረጃ በምንም መልኩ ውሸት መሆን የለበትም፤ ከይዘት እና ሰዋሰዋዊ ስህተቶች የጸዳ መሆንም አለበት።
- የተሟላ መልእክት፡- መረጃ ለውሳኔ መሰረት ነው። ያልተሟላ መረጃ ወደ የተሳሳተ ውሳኔዎች ሊመራ ይችላል።
- ያልተንዛዛ መልእክት፡- የሚላከው መልእክት አጭርና የተደራጀ መሆን

አለበት። ይህም ቀጥተኛ ትርጓሜ እንዲሰጠውና የሚፈለገው እርምጃ እንዲወሰድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

- የመልእክት ተዓማኒነት:- መልዕክት ላኪው የሚያስተላልፈው መልዕክት ሁሉ እውነተኛ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። መልእክቱ ትክክለኛ ከሆነ ተቀባዩ በላኪው ላይ እምነት ይኖረዋል።
- ተቀባዩን ከግምት ማስገባት:- ላኪው የተቀባዩን አመለካከት፣ ቋንቋ፣ እውቀት፣ የትምህርት ደረጃ እና አቋሙን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቅበታል።
- አክብሮት:- የሚሰናዳው መልእክት ለተቀባዩ ያለውን ክብር የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል።

## 6.4.2 ባህልን መናበብ

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

- በባህሎች መካከል ያለ ተቃርኖን መፍታት ማለት ምን ማለት ነው?
- በአካባቢያችሁ ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን አለመግባባቶች እንዴት ይፈታሉ?

የባህል መናበብ ማለት ተከታታይነት ባለው አካሄድ አለመግባባቶችን የመፍታት ልምዱ ወይም ችሎታው ያለው ሦስተኛ ወገን ሁለቱን ተፋላሚ ወገኖች ወደ አንድ በማምጣት አንዳች ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ወይም የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግን የሚመለከት ሂደት ነው። የባህል መናበብ በግንዛቤ እጥረት የሚከሰትን አለመግባባት ለማስቀረት የሚረዳ ነው። የባህል መናበብ ለሁለቱም ቡድኖች የማይወግን ሌላ ሦስተኛ ወገን ሲሆን ሁለቱ ተጻራሪዎች ባልተግባቡበት ጉዳይ ተቀራርበው እንዲነጋገሩና ልዩነቶቻቸውን እንዲፈቱ የሚያቀራርበው አካል ነው። ይህ አመቻች በቋንቋና ባህል የተነሳ የተፈጠረው ቀዳዳ እንዲደፈን ለመርዳት አገናኝ ድልድይ መሆኑ ላይ ልምድ ያካበተ መሆን አለበት።

ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን አለመግባባቱ በመካከላቸው የተፈጠረባቸው አካላት

ሁሉ ግጭቶቻቸውን ለማስወገድ ሙሉ ፍላጎት ያላቸውና እውነተኛ መፍትሔ ለማስገኘት ቁርጠኛ መሆናቸው ወሳኝ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥም የመፍትሄ ሃሳቡን የሚያደናቅፉ ተግዳሮቶችን መረዳትም አስፈላጊ ነው።

በባህል አለመናበብ የተነሳ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን የማስታረቅ ሥርዓት ጠቀሜታ፡-

- በባህል መካከል የሚፈጠሩ እንቅፋቶችን በመቀነስ የተሻለ ግንኙነት እና መግባባትን ማምጣት፤
- ሁለቱ ወገኖች ሀሳባቸውን እንዲገልጹ እድል መስጠት፤
- በሶስተኛ ወገን አጋዥነት አለመግባባቶችን መፍታት፤
- በህብረተሰብ ውስጥ አቃፊነትንና ግልፅነትን ማሳደግና የመሳሰሉት ናቸው።

## 6.4.3. ንቁ መስተጋብር መፍጠር

የግንዛቤ ጥያቄ

- ንቃት ያለው መስተጋብር ምንድን ነው?

የነቃ መስተጋር ባለቤት መሆን ማለት አብሮ በመኖር ሂደት ውስጥ የምንፈልገውን በግልፅ መናገር መቻል ማለት ነው። ይህም በተፈጥሮ የሚወረስ ችሎታ ሳይሆን በመማር ልንቀዳጀው የምንችለው ችሎታ ነው። ፍላጎታችንን በመግለጹ ላይ አቅም የሚያንሰን ከሆነ ስለጉዳዩ የቀሰምነው ዕውቀት ብቃት ከሌላቸው ሰዎች ሊሆን ይችላል።

በነቃ መስተጋብር መፍጠር ውስጥ ዋናው ጉዳይ ሌላው ሰው ፍላጎታችንን እንዲያሟላልን ስንፈልግ ያለንን የተለየ ባህሪ በተቻለ መጠን ቀላል ማድረግ ነው። አንዳንድ ሰዎች በሆነ ጉዳይ ስጋት ሲገባቸው ጉልበትን በመጠቀም አንዳች ነገር ማግኘት እንዳለባቸው ያምናሉ። ብዙውን ጊዜ ይህ ዘዴ ተቃራኒው ውጤት የሚገኝበት ነው። ፍላጎት የሚያመለክተው ተቀባዩ ከሰጪው ያነሰ ዋጋ ያለው መሆኑን ነው። ስለሆነም ሰጪ ሰው በሌሎች ላይ ለመወሰን መብት

እንዳለው ያመለክታል። ይህ መርህ በንግዱ አለም ባሉ አጋሮች፣ በስራ ባልደረቦች፣ በጓደኞች፣ በልጆች እና በቤተሰብ መካከል እንዲሁም በሌሎች ሁሉ ላይ ይተገበራል።

ስለባህላቸው በቂ እውቀት ወይም ልምድ የሌለን ከሆነ የተለያዩ ባህሎች ያሏቸውን ሰዎች ለመረዳት በጣም አስቸጋሪ ሊሆንብን ይችላል። በባህሎች መካከል መስተጋብር የመፍጠር ክህሎት በረዥም ዓመታት ሂደት ውስጥ ስለተለያዩ አመለካከቶች፣ ባህሪያት፣ ርዕዮተ አለሞችና ልማዶች በመቅሰም ብቻ የሚጎለብት ነው። ስለሆነም የባህል አስታራቂ እንዲሆን የምንመርጠው አዋቂ ሰው ባህላችንን በተመለከተ የዳበረ እውቀትና ልምድ ያካበተውን መሆን አለበት።

የነቃ መስተጋብር ባለቤት የመሆን ጉዞን የሚያሳልጥ ባለአራት ደረጃ ቀላል ሂደት:-

1. ስሜታችን እንዲጎዳ ያደረገውን ሁነት መለየት። ምን ተከስቶ እንደነበር በቀጥታ መግለጽ። ክስተቶችን ልክ እንደገለልተኛ ተመልካች በመሆን ማሳየት፡፡ ለምሳሌ፣ "ጓደኛዬ በሰዓቱ የሚመጣ አይደለም" ከማለት ይልቅ "ከጓደኛዬ ጋር 7:00 ላይ ለመገናኘት ተቀጣጥረን ነበር፤ ነገርግን እስከ 7:30 ድረስ አልመጣም" ማለት።
2. ለስሜታችን ኃላፊነት መውሰድ። ስሜታችንን በምንገልጽበት ጊዜ የሚሰማንን ስሜት ሳንደብቅ በግልጽ ለመናገር የሚረዱንን ቃላት እንምረጥ ፣ ለምሳሌ "ሀዘን፣ ብቸኝነት፣ ብስጭት ወይም ቅናት ይሰማኛል" ማለት። ተጠቂነትን ከሚያጎሉ ቃላት እንራቅ፤ ለምሳሌ "በጣም ተንቄያለሁ፣ ተከድቻለሁ፣ እኔ በጣም ተረስቻለሁ..." ከመሳሰሉት። እነዚህ ቃላት ሌላ ሰው በስሜታችን ውስጥ ሚና እንዳለው ያመለክታሉ። ለስሜታችን ኃላፊነትን ስንወስድ በህይወታችን ውስጥ ያሉ ሰዎችን ከመውቀስ ይልቅ የተሰማንን ፊትለፊት እያሳወቅን ነው ማለት ነው።
3. የሚያስፈልገንን አለማግኘታችንን እንለይ። በህጻንነታችን ስሜታችንን

ለይተን በራሳችን መግለጽ የማንችል በመሆናችን ተንከባካቢዎችን እንጠብቅ ነበር። በልጅነታችን ወቅት ደግሞ ጓደኞቻችን በራሳቸው አውቀው የሚያስፈልገንን እንዲሰጡን እንጠብቃለን። ይህ ምናልባት አንዳንዴ ሊሳካ ይችላል። ነገር ግን፣ ፍላጎቶቻችን በትክክል ሊሳኩ የሚችሉት በራሳችን ከለየናቸውና እንዲፈጸሙልን ደግሞ በግልጽ ለሌሎች ከገለጽናቸው ወይም ከተናገርናቸው ነው።

4. የምንፈልገውን እንጠይቅ። ፍላጎታችንን ሊያሟሉ የሚችሉት የተለዩ ልማዶች ወይም ተግባራት የትኞቹ ናቸው? ለምሳሌ ጓደኞቻችን የበለጠ ትኩረት እንዲሰጡን ከፈለግን ከእኛ ጋር ብዙ ጊዜያቸውን እንዲያሳልፉ እንጠይቃቸው፣ በእረፍት ጊዜ አብረውን አየር እንዲቀበሉ ወይም ወደ ሜዳ ሄደው አብረውን ኳስ እንዲጫወቱ እንጋብዛቸው። ፍላጎታችንንም በተራ ንግግር ሳይሆን በጥያቄ መልክ እንግለጽ (አየር እንቀበል? ለምን ኳስ አንጫወትም?)። ብዙ ሰው በተፈጥሮው ተራ ንግግሮችን ያለመቀበል ዝንባሌ አለው። ጥያቄዎችን መመለስ ስንችል በራስ መተማመናችን እያደገ ይሄዳል። ይህንን አካሄድ መከተል ሁልጊዜም ፍላጎታችን እንደሚሟላ ማረጋገጫ ባይሆንም ምቾት በሚሰጥና እና ዘና ባለ ስሜት ውስጥ እንድንቆይ ያደርገናል።

## ተግባራ 5

ባህላዊ ማንነትህ/ሽ ምን አይነት መልኮች በውስጡ እንዳሉት ተመልከት/ች። ከጓደኛህ/ሽ ጋር በመሆን ስለባህላዊ ማንነትህ/ሽ ከዚህ በታች ባለው መልኩ ጻፍ/ፊ።

1) የባህል ማንነቴ፡- ________________

2) እኔ ያለኝ ልማድ፡- ________________

3) አስፈላጊ ማሳያዎች፡- ________________

4) በባህሌ የምመገባቸው ምግቦች፡- ________________

5) የምደሰትባቸው ክብረ በዓላት፡- ________________

6) ለመጎብኘት ተገቢ የሆኑ ቦታዎች፡- ______________________

7) የምለብሳቸው አልባሳት፡- ______________________

8) ታዋቂ ጥበብ፡ ______________________

9) ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች፡- ______________________

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የባህል ትስስር የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት። ከነዚህ ጠቀሜታዎች መካከልም ጥቂቶቹ አዲስ ባህል ማግኘት፣ አዲስ ልምድ መቅሰምና የተሳሳቱ አመለካከቶችን ማስቀረት የመሳሰሉት ናቸው። ሰዎች የተለያየ ባህል ካላቸው ጋር መስተጋብር በፈጠሩ መጠን ከባህላቸው ጋርም ትውውቅ እያደረጉ ይመጣሉ። ይህም በየባህሎቹ ያሉ አዳዲስ ነገሮችን እየተማማሩ እንዲሄዱ ያስችላቸዋል።

ሉላዊነት ግለሰቦችና ማህበረሰቦች በመልከዓምድራዊ አቀማመጥና ርቀት የማይገደቡ መሆናቸውንና በአለማቀፍ ደረጃ ማህበራዊነት ጠንካራ መሰረት እየጣለ መምጣቱን ያመለክታል። የአለማቀፋዊነት መጎልበት በባህልና ማህበረሰብ መካከል የእረስበርስ ትስስርና መደጋገፍ እንዲኖር ያደርጋል። ይህም በሉላዊነትና በባህል መካከል ህብረት መኖሩን ያመላክታል።

የባህል መስተጋብር ማሳያዎች የሚባሉት፡- ውጤታማ መስተጋብር፣ የባህል መናበብ፣ ንቃት ያለው መስተጋብር እና የመሳሰሉት ናቸው።

ውጤታማ መስተጋብር ማለት ሀሳብን፣ እውቀትን እና መረጃን በመለዋወጥ አንድ አላማ ወይም ግብ በተገቢው ሁኔታ እንዲፈጸም ማድረግ ነው። የባህል መናበብ ማለት ደግሞ ቀጣይነት ባለው አካሄድ ሦስተኛው ወገን ባለው ስልጠና ወይም ግጭቶችን የመፍታት ልምድ ሁለቱን የተኳረፉ/የተጋጩ አካላት በማቀራረብ የጋራ እሳቤ እንዲይዙ ማድረግ ነው። ይህም በግንዛቤ እጥረት የተነሳ የተፈጠረን የባህል ግጭት ለማስቀረት የሚረዳ ነው።

ንቃት ያለው መስተጋብር ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ በህይወታች ውስጥ የምንፈልገውን ነገር በግልጽ ከመናገር/ከመጠየቅ የሚመነጭ ነው።

# የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ትእዛዝ 1፡** የሚከተሉት አረፍተነገሮች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት፣ ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ/ሽ!

1) ቴክኖሎጂ ለባህል ልውውጥ መዳበር አስተዋፅዖ አድርጓል።
2) ባለፈው ክፍለ ዘመን ርቀት ማህበራዊ ግንኙነቶችን ገድቦ ነበር።
3) የተሳሳተ አመለካከት መሬት ላይ ያለውን እውነታ እንዳንረዳ ያደርገናል።
4) የኔ ባህል ይበልጣል ማለት በባህሎች መካከል ትስስር ለመፈረጠር እንቅፋት ነው።

**ትዕዛዝ 2:** ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ/ጪ።

1) በአሁኗ አለማችን አገሮች እንደ አንድ መንደር የተቆጠሩት ለምንድን ነው?
   (ሀ) የባህል ልዩነት
   (ለ) የትምህርት መስፋፋት
   (ሐ) የመገናኛ ብዙሃን እድገት
   (መ) በሀብታና እና ደሃ መካከል ልዩነቱ መስፋት
2) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አብዮት ያመጣው የትኛው ነው?
   (ሀ) ስልክ    (ሐ) ኢንተርኔት
   (ለ) ፋክስ    (መ) ሁሉም
3) ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው የባህል መስተጋብር ማሳያ ይሆናል?
   (ሀ) ውጤት ያለው ተግባቦት    (ሐ) ንቁ መስተጋብር መኖር
   (ለ) የባህል መናበብ    (መ) ሁሉም
4) ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የሰው ልጆችን ተግባቦታዊ መስተጋብር ከማስጠበቅ አንጻር ማህበራዊ ፍላጎትን የሚያሟላ አይደለም፡-
   (ሀ) መታቀፍ    (ሐ) መገለል
   (ለ) ፍቅር    (መ) ቁጥጥር

5) ከተጠቀሱት መካከል አንዱ የውጤታማ መስተጋብር ማሳያ ያልሆነው የቱ ነው?

(ሀ) የተሟላ መልዕክት (ሐ) እውነተኛነት

(ለ) ትክክለኛ መልዕክት (መ) ተዓማኒነት ማጣት

**ትዕዛዝ 3: ባዶ ቦታዎችን ይሙሉ**

(ሀ) በባህል መካከል ያለው ትስስር አንዳንድ ጊዜ ____________________ ይባላል።

**ትዕዛዝ 4፡ ባጭሩ መልሱ**

(ሀ) የባህል መናበብ ጠቀሜታ ምንድን ነው?